# ሞት ወደ ዓለም እንዴት መጣ?

እግዚአብሔር አምላክ አባታችንን አዳምን ፈጥሮ በተድላ ገነት እኖረው ፤ ከነፋናበነ የምታስታውቀውን የዛፍ ፍሬ እንዳይነካ ( እንዳይበላ) ከለከለው (ዘፍ ፪ ፡ ፲፯) ።

ሔዋን የሰይጣንን ተንኮል ሳታውቅ ምክሩን ተቀብላ አዳም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲተላለፍና ከኃጢአት ላይ እንዲወድቅ አደረገችው (ዘፍ ፫ ፡ ፩—፮) ።

እግዚአብሔርም በአዳምና በሔዋን ተቆጥቶ ረገማቸው ፤ ሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ፈረደባቸው (ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ፤ ኩፋሌ ፡ ፬ ፡ ፳፫)። ከገነት አስወጥቶ ወደዚች ምድረ ፋይድ አባረራቸው (ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፳፬)።

አዳምና ሔዋን ፤ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ፡ ዘራቸውና ትውልዳቸው ሁሉ በዚህ ፍርድ መሠረት በሞተ ሥጋ ወደ መቃብር ፡ በሞተ ነፍስ ወደ ሲኦል መውረድ ግዴታ ሆነባቸው ።

፭ሺ፭፻ ዘመን ፍጻ ተፈጽሞ አምላክ ወልደ አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ተሰቅሎ ሞቶ ተነሥቶ ዓለምን በደሙ እስከሚያድነው ድረስ ሞት የበደሉትንም ሆነ ያልበደሉትን በአንድነት ገዝቶአቸዋል ።

በኋላ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ሞተ ነፍስ ቢጠፋም ሞተ ሥጋ አልቀረም ። ሞተ ነፍስም ቢሆን ከአዳም በተወረሰው የዘር ኃጢአት ምክንያት መተላለፉ ቀረ እንጂ እየአንዳንዱ ሰው በፈጸመው በደልና በሠራው ኃጢአት በንስሐ ካልታደሰ ሞተ ነፍስ ያገኘዋል ። (ሮሜ ፭ ፡ ፲፪ ፤ ቆላ ፩ ፡ ፳፩ ፤ ሉቃ ፡ ፲፫ ፡ ፲፩—፳፰ ፤ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፱) ።

በዚህ ዓይነት ሞተ ሥጋም ሆነ ሞተ ነፍስ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረሱ ትእዛዙን በመጣሱ ራሱ ገንዘብ ያመጣው ጣጣ እንጂ እግዚአብሔር የባሕርዩ አድርጎ ለሰው አልፈጠረበትም ነበር ።

ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፈ ጥበብ "እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረም ትዋረድ ይሆን ዘንድ ፍጥረትን (ሰውን) ፈጥሮዋልና ፤ የሰዎች ጥፋት ደስ አያሰኘውም። በእጃችሁ ሥራ ሞትን አታምጡ ፡ የሰውን መፈጠር ለድኅነት ነውና በእነርሱ ዘንድ ሁሉን የሚያጠፋ የሞት መርዝ ኃጢአት አልነበረምና ሕይወት የሚታልፍ ስለሆነች ፤ ለመቃብርም በዚህ ዓለም ግዛት አልነበረምና እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን በቃል ጠፉት ባልንጀራም አደረጉት ፡ በዚህም ጠፉ» ይላል (ጥበ ፡ ሰሎ ፡ ፩ ፡ ፲፫-፲፮ )

ሞት ወደዓለም እንዴት እንደመጣ ጠቢቡ ሰሎሞን ከዚህ በላይ እንደ

ገለጸው ሁሉ ሞት በሰዎች ኃጢአትና በደል የመጣ መሆኑ ታውቋል ።

«ተመልከት ፡- ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን ፡ ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ ፡ በሕይወትም እንድትኖር እንድትበዛ አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት ምድር እንዲባርክህ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወደው ዘንድ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ ትእዛዙንና ሥርዓቱን ፍርዱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ ። ልብህ ግን ቢስት አንተም ባትሰማ ብትታለልም ለሌሎችም አማልክት ብትሰግድ ብታመልካቸውም ፈጽማችሁ እንደምትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ ፡ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ በምትገባባት ምድር ዘመ

ናችሁን አታስረዝሙም ፤ በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን ፤ በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ ፤ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ ፤ እግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው ዘንድ ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ" ተብሎ በኦሪት ተጽፎአል ። (ዘዳ ፡ ፴ ፡ ፲፭-፳)

በሐዲስ ኪዳንም ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ ሞት በኃጢአት ምክንያት ወደ ዓለም መምጣቱን በየመልእክታቱ ገልጾ አስተምሮአል ። ይህም ሞት በሰው ልጅ ሁሉ ላይ የተወሰነ ስለሆነ ማንንም ከማን ሳይለይ የበደሉትንም ያልበደሉትንም ገዝቷቸዋል።ስለዚህ «በአንድ ሰው በደል ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ ፤ ስለዚህም በሰው ሁሉ ላይ ሞት መጣ በዚህም ኃጢአት ምክንያት ከአዳም እስከ ሙሴ የበደሉትንም ያልበደሉትንም ሞት ገዛቸው ሁሉ በአዳም አምሳል ተፈጥሮአልና» (ሮሜ፡ ፭ ፡ ፲፪—፲፬)።

ሞት በኃጢአት ምክንያት ወደ ዓለም እንደመጣ ከዚህ በላይ በአጭሩ ለመረዳት ችለናል ።

በመሠረቱ ሞት ስንል ምን ማለታችን ነው ? ሞት ስንል በመጀመሪያ የምናየው ፤ የሥጋንና የነፍስን መለያየት ነው ። ሰው ሞተ በምንልበት ጊዜ ሕያውና ተንቀሳቃሽ አድርጋው በውስጡ የምትኖር ሕያውት ነፍስ ከሥጋው ተለየች ማለታችን ነው ።

ሕያውት ነፍስ ከሥጋ በምትለይበት ጊዜ ደም በመላ ሕዋሳት የመዘዋወር ሥራውን ያቋርጣል ። በደመ ነፍስ የሚንቀሳቀሰው ሰውነትም ሥራውን ያቆማል ነፍስ በደም ታድራለች ተብሎ ተጽፎአልና (ዘፍ ፱ ፡ ፬ ፡ ዘሌ ፡ ፲፯ ፡ ፲፩ ፡ ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፶)

በኃጢአት ምክንያት የሚመጣው ሞት ፤ በሞተ ሥጋ ብቻ የሚወሰን አይደለም ። ሞተ ነፍስንም ያስከትላል ። ይኸውም ሁለተኛ ሞት ማለት ነው ። ሁለተኛ ሞት የተባለውም የነፍስ ከእግዚአብሔር መለየትና ዘለዓለማዊ የሆነ ኩነኔ ገሃነምን መቀበል ነው ። ስለሆነም ሞተ ነፍስ እንደሞተ ሥጋ ሁሉን አያጠቃልልም ። ሞተ ነፍስ የሚፈረደው በክርስቶስ በማያምኑ፤ሕጉን በማይጠብቁ ትእዛዙን በማይፈጽሙና ንስሐ በማይገቡ ሰዎች ላይ ብቻ ነው ።

> "ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ ፤ ሰውነታቸውን
> የሚያሳድፉ ፤ ነፍሰ ገዳዮች ፤ የሚሰስኑ ፤ ሥራይ
> የሚያደርጉ ፤ ጣዖት የሚያመልኩ ሐሰት የሚናገሩ
> ቅጣታቸው በእሳትና በዲን ጉድጓድ ይሆናል ፤
> ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው" (ራእ ፳፩፡ ፫፡ ፰ ፡ ፲፱)

በቅዱሳት መጻሕፍት የታዘዘውን አለመፈጸምና የስነ ምግባር ጉድለትም ሞተ ነፍስን እንደሚያመጣ በቅዱስ ወንጌል ተጽፎአል ። (ማቴ ፡ ፳፩፡፯፭)

ሞት ከሞተ ሥጋና ሞተ ነፍስ ሌላም የሰውን ልጅ ስነ ምግባር በተመለከተ የተለያየ ትርጉም አለው ። በሃይማኖት ጸንተው ፤ በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ የማይኖሩ ፤ መልካሙን ነገር አውቀው የማይሠሩና በኃጢአት መንገድ የሚጓዙ ሁሉ በሕይወት እያሉ ሙታን ሕሊና ይባላሉ (ማቴ ፡ ፰ ፡ ፳፪ ) ።

የሞት ትርጉሙ መለየት መሆኑ ታውቋል ። ስለሆነም ታላላቅ የሃይማኖት አባቶችና መንፈሳውያን ሰዎች የወዲሁን ዓለም በወዲያኛው ዓለም ለውጠው የጽድቅ ወራሾች ለመሆን ዓለምንና በዓለም ያለውን

ሁሉ ትተው እግዚአብሔርን ለማገልገል ሰውን በጸሎታቸው ለመርዳት ይወስናሉ ። እንደነዚህ ያሉት ደጋግ ሰዎች ከዓለም ሥራ መለየታቸውን ለመግለጽ ራሳቸውን እንደሞተ አድርገው ይቆጥራሉ ። ይህንንም ሐዋርያው ቅ/ ጳውሎስ "ዓለም በኔ ዘንድ የሞተች ናት ፥ እኔም በዓለም ዘንድ የሞትኩ ነኝ" በማለት አረጋግጦታል ። /ገላ፡ ፮፡ ፲፬/

የሞተ ሥጋና የሞተ ነፍስ ሁኔታ ከዚህ በላይ በአጭሩ የተዘረዘረው ሆኖ ሳለ የሰው ልጆች ቀደም ሲል በኃጢአታቸው ሞትን ወደ ዓለም ማምጣታቸው አልበቃ ብሎ በዘመናችን ሞትን በተለያየ መልኩ በራሳቸው ላይ ሲያመጡ ይገኛሉ ።

ይኸውም ጽንስን በማስወረድ ፤ የራሳቸውንም የልጆችንም ሕይወት ያጠፋሉ ።

በመታነቅ ፥ መርዝ በመጠጣትና በተለያዩ ድርጊቶች ሕይወታቸውን ያሳልፋሉ፤ከዚህም ሁሉ ጋር ሰዎች በተፈጥሮ ሕማምና ጦርነትን በመሰለ በሰውነታቸው ላይ በሚደርስ አደጋ ሲሰቃዩ በራሳቸው ወይም በሌላው ሕይወታቸው እንዲአልፍ የሚያደርጉም አሉ ። ይህም ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት የተከለከለና በቤተ ክርስቲያን የተወገዘ ነው በዚህ ዓይነት አሟሟት ሕይወታቸውን የሚያጠፉ ሁሉ በሃይማኖት ትምህርት ተቀባይነት የላቸውም ። በሞቱም ጊዜ በሕግና በሥርዓት ኖረው በክብር ለሞቱ ሰዎች የሚፈጸመው የቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ፍትሐትና ሌላውም ሥርዓት ሁሉ አይፈጸምላቸውም ። (፪ ሳሙ ፩ ፡ ፩-፲ ፤ ማቴ ፡ ፳፯፡፭)

በዚያም ሆነ በዚህ ሞተ ሥጋንና ሞተ ነፍስን ለማምጣት ፥ ለዕድሜአቸው ማጠርም ሆነ መርዘም ምክንያቶቹ ራሳቸው ሰዎች መሆናቸውን እናያለን ። በቅዱስ መጽሐፍ እንደምንመለከተው በሺህና በብዙ መቶ ይቆጠር የነበረው ዕድሜ ወደ መቶ ሃያ ፥ ከዚያም ወደ ሰባ እያሽቆለቆለ የመጣው ከሰዎች ጥፋት፤ኃጢአትና በደል የተነሣ መሆኑ ተገልጾአል ። በዘመናችን ሰዎች ሞትን በተለያየ አቅጣጫ ለመጋበዝ የሚያደርጉት ጥረት ሁሉ ከዚያው ከሰባና ከሰማንያውም ለማሳነስና ለማሳጠር ነው ።
(ዘፍ ፡ ፭ ፡ ፳፯ ፡ ፮ ፡ ፫ ፡ መዝ ፡ ፹፱ ፡ ፲ ፡ ፲)

ስለዚህ ከዚህ በላይ በተለያየ ሁኔታ በተገለጡት የአሟሟት ዓይነቶች ሕይወትን በማጥፋት በሥጋም ሆነ በነፍስ ከሚደርሰው ቅጣት ለመዳን ቅዱሳት መጻሕፍት በሚሰጡት ትምህርትና ምክር መመራት የክርስቲያኖች ሁሉ ግዴታ ነው ።

ክርስቲያኖች ሊፈሩትና ሊጠነቀቁበት የሚገባው ሞትም ሞተ ሥጋብቻ ሳይሆን ሞተ ነፍስን ስለሆነ በጊዜያዊ ችግሮችና በኃላፊው ዓለም ወደ ቀቢጸ ተስፋ መድረስና በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረ ሰውነትን ማጥፋት እንደማይገባ ቤተ ክርስቲያን አበክራ ትመክራለች ።

## ማማወት (ማጋጠም)

ሰው ከዚህ ዓለም በሞት በሚለይበትና ጹሕተ ነፍስ በሚሆንበት ጊዜ በሰውነት ላይ በሚደርስ ጣር ጋር መጨነቅና መወራጨት አለ ። በዚህም ምክንያት ሟች በመወራጨት ላይ በነበረበት ሁኔታ ያርፋል ።

በሞት ጊዜ ጣር ጋር የማያገኛቸው መጨነቅና መወራጨት የማይኖርባቸው ደጋግ ሰዎች ይኖራሉ "በቅንነት የሄደ በአልጋው ላይ ያርፋል" ተብሎ እንደ ተጻፈ በጎ ዕረፍትን የሚታደሉ ብዙዎች ናቸው ።

ይሁን እንጂ ሥጋ ነፍስ ከተለየችው በኋላ የማይሠራ የማይንቀሳቀስ በድን ስለሆነ የሰውነቱን ክፍሎች ማስተካከልና ማጋጠም ያስፈልጋል ። የተገለጡት ዐይኖች መክደን፤የተከፈተው አፍ መግጣጠም ያስፈል

ጋቸዋል ፤ የታጠፉ ወይም ያለአግባብ የተዘረጋጉ እጆችና እግሮች በአግባቡ እንዲሆኑ ማድረግ ያሻል ። (ዘፍ ፵፱ ፡ ፴፫ )

ነፍስ የተለየችው ሰውነት ራሱን የማይቆጣጠር በመሆኑ ከሰ ውነት የሚወጡ ልዩ ልዩ ነገሮች (ሬሣ ሽሽ) ተወግደው በድኑ በንጽሕና መዘጋጀት ይኖርበታል ።

ይህም የሚፈጸምበት ምክንያት ከብሉይ ኪዳን ተያይዞ የመጣ ተወራራሽ ትውፊት ከመሆኑም በላይ የክርስቲያኖች አካል በክርስቶስ የከበረና ትንሣኤ ዘለክብርን የሚጠብቅ ስለሆነ ነው ።

## ሕጽበትና ሽቱ መቀባት

ሰው በሞት ጊዜ ሰአካሉ ንጽሕና የሚገባው ጥንቃቄና ዝግጅት ይደረጋል ። መጀመሪያ በተራ ውሃ ይታጠባል ። ቀጥሎም በተጸለየበት ውሃ ይታጠባል ፤ በውሃው ላይ የሚጸለየውም ጸሎት ፩ኛ በእንተ ድኅነተ ነፍስ (ስለነፍስ ድኅነት) የሚለው መስተብቍዕ ፪ኛ መቶ ሃምሳው መዝሙረ ዳዊት ፫ኛ ዐሥራ አምስቱ መሐልየ ነቢያት ፬ኛ አምስቱ መሐልየ ሰሎሞን ፭ኛ ወንጌል ዮሐንስ ፮ኛ መልክአ ማርያምና አንቀጸ ብርሃን ነው ።

ይህም ሥርዓት ኅጽበት የሚፈጸምበት ምክንያት ሙታን በሰውነታቸው መጉደፍ መገሳቆል ስለሚያገኛቸው ሳያጥቡና ሳያነጹ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊያገቧቸው እንደማይገባ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተደነገገ በመሆኑ ነው ። ይህም ሥርዓት በሐዋርያት ዘመን ሲፈጸም የኖረ ነው ። በግብረ ሐዋርያት ፱ ፡ ፴፮ እንደሚነበበው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ከሞት ያስነሣት ጣቢታ የተባለችው ሴት ከሞተች በኋላ ሥርዓተ ሕጽበት ተፈጽሞላታል ።

ሰው በሞት ጊዜ ከላይ እንደተገለጠው ሕጽበትና አስፈላጊው የንጽሕና ዝግጅት ሁሉ ከተፈጸመለት በኋላ ሽቱ ያርከፈክፉበታል።ይህም ሥርዓትና ልማድ በብሉይ ኪዳን ከቀደምት አበው ተያይዞ የመጣ ነው ።

በሐዲስ ኪዳንም የቤተ ክርስቲያን መሠረት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማርያም እንተ ዕፍረት መዓዛው የባፈጠ ሽቱ አምጥታ እግሩን በቀባችው ጊዜ «- - - - ለምቀበርበት ቀን አዘጋጅታዋለች» በማለት የነበረውን ሥርዓት ጠቅሶ ለደቀ መዛሙርቱ ነግሮአቸዋል።(ሉቃ ፳፫ ፡ ፶፮ ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፯) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለድኅነተ ዓለም በሞተ ጊዜ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ይህን የሽቶ ማርከፍከፍ ሥርዓት ፈጽመውለታል ። (ዮሐ ፲፱ ፡ ፴፱)

— በብሉይ ኪዳን የነበረ ሥርዓት በመሆኑ

- የሙታኑ አስከሬን ሥርዓተ ቀብር እስከሚፈጸምለት በቤትና በቤተ ክርስቲያን ስለሚቈይ በንጽሕና ለመጠበቅ ፤

- መልካም ሽቱ የመልካም ስነ ምግባር ምሳሌ ስለሆነ ፤

- በምግባርና በሃይማኖት ጸንተው ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩ ክርስቲያኖች ሥጋቸው ፈርሶ በስብሶ በመቃብር የማይቀርና ነፍሳቸውም በመዓዛ ገነት የምትኖር መሆኑን ለማመልከት ነው ።

# ግንዘትና ክፈን

የሰው ልጅ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ አካሉ ታጥቦ ሽቱ ተቀብቶ (ተርክፍክፎ) የሰውነቱ ክፍሎች እንደሚገባ ተገጣጥመውና ተስተካክለው የእግሩና የእጁ ጣቶች በፈትል ታስረው በአዲስ ልብስ (ከፈን) ተጠቅልሎ ይገነዛል። በልብሰ መግነዙም ላይ የሚጸለይ ጸሎት አለ ። ጸሎቱም «ወላዲተ አምላክ ፣ ወላዲተ እግዚአብሔር ፣ ወላዲተ መድኅን ፣ ወላዲተ ሕይወት ፣ ወላዲተ ክርስቶስ ፣ ወላዲተ ኢየሱስ ፣ ወላዲተ ዐማኑኤል - - - » የሚለው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎት ነው ።

የአገናነዙም ሥርዓት በክርስትና ሃይማኖት የተለያየ ማዕርግና ትርጉም አለው ።

ሟች ካህን ከሆነ የክህነት ቀሚሱን እንደለበሰ እጆቹ በትእምርተ መስቀል ተመሳቅለው በአዲስ ልብስ ይገነዛል ። «መስቀሌን ተሸክሞ ያልተከተለኝ ሊያገለግለኝ አይችልም» ባለው መሠረት በሥልጣነ ክህነቱ ምእመናንን ይባርክና ነገረ መስቀሉን ያስተምር እንደነበር ለማዘከር ነው።

በድኑ በአዲስ ልብስ ከተጠቀለለ በኋላ በሦስት ክር (ማዕተብ) ይታሰራል ። በተጨማሪም ሰባት ትእምርተ መስቀል ያለበት ማዕተብ (ክር) ተሠርቶ ከሰባት ቦታ ላይ ይቋጠራል ። ይኸውም አንዱ በራስ ፤ አንዱ በእግር አንዱ በቀኝ አንዱ በግራው ሦስቱ በመካከል ሆኖ ይቋጠራል ። ይህም ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ ዐሥራ ሁለት መብራት ይበራል ። መብራትም የሚበራበት ምክንያት ከዚህ የጨለማ ዓለም ወደ ብርሃን ዓለም መሄዱን ያመለክታል ።

ሟቹ መነኮስ ቢሆን እጆቹን በዐይኖቹ ላይ ጭኖ ይገነዛል ። ይህም ሟቹ መነኮስ በዚህ ዓለም በሕይወተ ሥጋ በነበረበት ጊዜ በዐይኖቹ የዚህን ዓለም ክፉ ነገር ከማየት ተአቅቦ አድርጎ መኖሩን የሚያመለክት ነው ። የፈትሉ ፣ የከፈኑና የመግነዙ የመብራቱም ሥርዓት ለቄሱ እንደ ተፈጸመ ለሁሉም በየመዓርጋቱ ይፈጸማል ።

ሟቹ ዲያቆን ሲሆን ግን እጆቹን ግራና ቀኝ አስተላልፎ በሠቅ (ቀበቶ) መልክ በትጥቅ መዋያው ላይ በማሳረፍ ይገነዛል ። ይህም የሚያመለክተው ዲያቆናት ፣ በሕይወት ዘመናቸው እንደ ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ለተልእኮ ሲፋጠኑ መኖራቸውን ነው ።

በድኑ እንደተለመደው በአዲስ የከፈን ጨርቅ ከተጠቀለለ በኋላ በሁለት ፈትል ክር (ማዕተብ) ይታሰራል ። በፈትሉ አስተሳሰር የሚደረገው የመስቀል ምልክት ለቄሱ እንደ ተደረገ ለዲያቆኑም ይፈጸማል ። ይህም በሚፈጸምበት ጊዜ ሰባት መብራት ይበራል ።

ሕዝባዊ ከሆነ ግን አውራ ጣቶቹ በፈትል ታስረው እጆቹን በብልቱ ላይ ጭኖ ይገነዛል ። ይህም በሕጋዊ ጋብቻ ተወስኖ መኖሩን የሚገልጥ ነው ። ሥርዓቱ ሁለቱንም ጾታ ሴትና ወንድን ያጠቃልላል ።

— በድኑም የሚታሰረው በአንድ ክር (ማዕተብ) ነው ለሕዝባዊ የሚበራው መብራት ዓራት ነው ።

ሴት በወሊድ ወይም በአራስነትዋ ጊዜ ብትሞት በአልወለደችበት በሌላ ልብስ ይገንዙአታል ። «ሞት ስላነጻት» ጸሎተ ፍትሐት እንዲደርስላት በድንዋ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመግባት አይከለከልም ።

ይህ ሁሉ ሥርዓትና ትውፊት በክርስትና እምነትና ትምህርት የታሪክ መሠረት ያለው ነው ። በቅዱሳት መጻሕፍትም የተጻፈ ነው ።

ሰው ሲሞት የአካሉን ክፍሎች በመልክ በመልኩ አገጣጥሞና አስተ ካክሎ ማዘጋጀት ከዚያም በኋላ መገነዝና መከፈን እንደሚገባ ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል ። የማርያምና የማርታ ወንድም አልዓዛር መቃብር በተነሣ ጊዜ የተጻፈው ታሪክ እንደሚያስረዳን ይኸው ሥር ዓት የተፈጸመለት እንደነበረ ያስረዳል ። «የሞተውም (አልዓዛር) እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደተገነዙ ወጣ ። ፊቱም በጨርቅ እንደተጠ መጠመ ነበር» (ዮሐ - ፲፩ ፡ ፵፬)

የቀድሞ ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ከተልባ እግርና ከሐር ፈትል በተሠሩ ልብሶች ተከፍነውና ተገንዘው ይቀበሩ ነበር ። ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመው ሥርዓት ግንዛትም ይኸው ዓይነት ነው ። «የኢየሱስንም ሥጋ ወስደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት» (ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፵) ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ለክርስቲያኖች የሚፈጸመው ሥርዐተ ግንዘት ይህንኑ ትውፊት የተከተለ ነው ።

## ኀዘንና ልቅሶ

ሥጋዊ ሞት የሕይወት ፍጻሜ ባለመሆኑ ቢታወቅም ማንኛውም ሰው ሲሞትበት ጊዜ ከዚህ ዓለም ተለይቶ ወደማይመለስበት ዓለም ሲሄድ የቅርብ ዘመዶቹ በማዘን ማልቀስ ማዘንና እንባ ማፍሰስ ልማድና ከተፈጥሮ ጋር የተያያዘ ጠባይ ነው ።

በመሆኑም ከጥንት ጀምሮ ብዙ ሰዎች ለሞቱ ወገኖቻቸው እንደ የዘመኑ ልማድና እንደየሀገሩ ባህል ልቅሶ እንዳለቀሱላቸው መዝሙረ ኀዘን እየዘመሩ እንደሸኙአቸው በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ሥፍራ ተገልጦአል ።

ያዕቆብ በምድረ ግብጽ በሞተ ጊዜ ልጆቹና ቤተሰቡ አልቅሰውለታል ። (ዘፍጥ ፶፻)ነቢዩ ሙሴና ካህኑ አሮንም ከዚህ ዓለም በተለዩ ጊዜ ሕዝበ እስራኤል አልቅሰውላቸዋል (ዘኁል - ፳ ፡ ፳፱ ዘዳግ ፴፬ ፡ ፰) ለመስ ፍኑ ለዮፍታሔ ልጅም ጓደኞችዋ ደናግል አልቅሰውላታል ።(መሳ፲፩ ፡ ፴፰) ንጉሥ ዳዊት ለሳኦልና ለዮናታን፤ነቢዩ ኤርምያስ ለንጉሡ ኢዮ ስያስ አልቅሰውላቸዋል ፥ እንባቸውንም አፍስሰውላቸዋል ፤ መዝሙረ ኀዘንም ዘምረውላቸዋል (፪፡ሳሙ ፩ ፡ ፲፩-፳፯ ። ፪ዜና ፡ ፴፭ ፡ ፳፭-፳፯) ሌላም ይህን የመሰለ በብሉይ ኪዳን ይገኛል ።

በሐዲስ ኪዳንም በሐዋርያት ዘመን በክርስቲያኖቹ ስነ ምግባር የታወቀች ነዳያን የሚወዱአትና የሚያፈቅሩአት ጣቢታ በመባል የም ትታወቅ አንዲት ሴት በሞተች ጊዜ ትረዳቸውና ትደግፋቸው የነበሩ ሁሉ ተሰብስበው አልቅሰውላታል። (የሐዋ፡ ፱-፴፱) ማርያምና ማርታም ወንድማቸው አልዓዛር በሞተ ጊዜ አልቅሰውለታል ። ወዳጆቹና ዘመዶቹ እንባቸውን አፍስሰውለታል ። ይልቁንም ይህ ሰው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጅ ስለነበረ ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን አልቅሶ ለታል ። (ዮሐ ፡ ፲፩ ፡ ፲፯-፴፯)

ይሁን እንጂ በክርስትና እምነትና ትምህርት ሥጋዊ ሞት የሕይወት መጨረሻ ባለመሆኑ ፥ ኀዘኑም ልቅሶውም ገደብና ወሰን አለው ። መሪር ልቅሶ ማልቀስና የቀቢጸ ተስፋ ኀዘን ማዘን ለክርስቲያኖች የተከለከለ ነው ። ይህን የሚያደርጉ በሙታን ትንሣኤ የማያምኑ አሕዛብ ናቸው ። ቅዱሳት መጻሕፍት ይከለክላሉ ፤ ቤተ ክርስቲያንም ታወግዛለች ። ክርስ ቲያኖች ከተፈቀደውና ከተወሰነው የኀዘንና የልቅሶ ልማድ ወጥተው ፤

ወደ ውግዘት እንዳይገቡ በየጊዜው ታስተምራለች መግለጫም እያወጣች ታስተላልፋለች ። መሪር ኀዘንና እንባ በሃይማኖት ትምህርት አለመፈቀዱ ብቻ ሳይሆን በጤንነት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት በየጊዜው ይገለጣል ።

ይህን በተመለከተ ቅዱሳት መጻሕፍትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት ትምህርትና ምክር ብዙ ነው፤በሞተ ሰው ኀዘን/ምክንያት መሪር ኀዘን ማዘን፣ የማይቋረጥ ዕንባ ማፍሰስ፣በሰውነት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ድርጊቶችን መፈጸም፣ ሙሾ እያወረዱ ደረትን መምታት ይህንም የመሰለውን ሁሉ መፈጸም እንደማይገባ ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ በአራቱ ጽፎአል ። «እናንተ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና በምድርም ላይ ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለርሱ ለራሱ ሕዝብ ትሆንለት ዘንድ እግዚአብሔር አንተን መርጦአልና ስለሞተው ሰው አካላችሁን አትንጩ ራሳችሁን አትላጩ ። »(ዘዳግም ፲፬ ፡ ፩-፪)

ጠቢቡ ሲራክም «መሪር ኀዘን ኃይልን የሚያደክም ስለሆነ የቀቢጸ ተስፋ ኀዘን እንዳይገባህ --- ልቅሶህን ተው ፤ መሪር ኀዘንና ትካዜ ለሞት ያደርሳል ። --- መሪር ኀዘንን ወደ ልቡናህ አታግባ ፤ የቀቢጸ ተስፋ ኀዘንን አርቃት ጥቅም እንደሌለባት እወቅ ። ራስህን ታሳዝናለህ ፤ የምትጠቀመውም ነገር የለም ። ---» (ሲራክ ፴፰ ፡ ፲፰-፳፫)

ከነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም ይህን የመሰለ ምክርና ትምህርት ተጽፎአል ። ነቢዩ ዳዊት የወለደው ሕፃን በታመመ ጊዜ ከዙፋኑ ወርዶ ልብሰ መንግሥቱን ጥሎ ማቅ ለብሶ አመድ ነስንሶ አዘኖ ጸለየም ። ሆኖም የሕፃኑ መሞት በእግዚአብሔር የተወሰነ ስለነበረ በሞተ ጊዜ ኀዘኑን ተወ ። ሕዝቡም ባህልና ልማድ እንደተለወጠ አይተው በጠየቁት ጊዜ«ሕፃኑ ሕያው ሳለ ይምርልኛል ሕፃኑም በሕይወት ይኖር እንደሆን ማን ያውቃል ? ብየ ጾምሁ ፣ አለቀስሁ ። አሁን ግን ሞቶአል ፣ የምጾመውስ ለምንድን ነው? በውኑ እንግዲህ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛልን ? እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም» ብሎ መልሶላቸዋል (፪ኛ ሳሙ ፲፪ ፡ ፳፩-፳፫) ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የክርስቲያኖች ኀዘንና ልቅሶ ወሰንና ገደብ እንዲኖረው እንጂ ተስፋ ትንሣኤን እንደማያምኑ እንደ አሕዛብ በቀቢጸ ተስፋ እንዳይሆን በመልእክቱ ጽፎአል ። « ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ሰዎች ደግሞ እንዳታዝኑ አንቀላፍተው ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሞተና እንደ ተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና ። » (፩ ተሰ ፡ ፬ - ፲፫)

ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም የቀቢጸ ተስፋ ኀዘን የማይገባ መሆኑን በሰፊው አትቶ በተግሣጽ መጽሐፉ አስተላልፎአል ።

«ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሞተላቸው መሆኑን የሚያምኑ ክርስቲያኖች ወገን በሞተባቸው ጊዜ የራሳቸውን ጸጉር ለምን ይነጫሉ? ሴትስ ቃልዋን ከፍ አድርጋ ለምን ትጮኻለች ? ከዚህ የከፋ ምን ውርደት አለ ? እንደ እነዚህ ያሉትን ሰዎች ለብዙ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመግባት ሊከለክሉአቸው ይገባል ። ከሞቱትም ይልቅ ለእነዚህ ሊያለቅሱላቸው ይገባል ፤ ሞትን ፈርተው ይደነግጣሉና የሙታንንም ትንሣኤ አያምኑምና ። --- መሪር ልቅሶ ማልቀስ ፣ የቀቢጸ ተስፋ ኀዘን ማዘንም የአሕዛብ ልማድ ነውና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሊገባ አይገባውም »በማለት ደረት መድቃትን ፊት መንጨትን ፣ አልቃሽ አቁሞ ማርገድን በአጠቃላይ ከክርስትና እምነትና ትምህርት ውጭ የሆነ ኀዘን ማዘን እንደማ

ይገባ በተግሣጹ ይመክራል ያስተምራል ። (ተግሣጽ አንቀጽ ፬ ገጽ ፴፱ -፵፯)

በፍትሐ ነገሥትም በፍትሕ መንፈሳዊ «ሰው በሞት ጊዜ እንደ አረማውያን አትሁኑ ልብሳችሁን አትቅደዱ ፣ ፊታችሁን አትንጩ አካላችሁን አታቁስሉ ፣ ደረታችሁን አትምቱ ፣ ራቁት አትሁኑ ልቅሶ አታዘውትሩ ፣ የራስ ጠጉራችሁን አትላጩ እግዚአብሔርን በትዕግሥት አመስግኑት ፣ እንደ ኢዮብ ትዕግሥተኞች ሁኑ ፣ አትዘኑ ፣ ሰው ሞቶ አይቀርም ፣ በኋላ በትንሣኤ መነሣቱን እመኑ ። በጌታችን በኢየሱስ ዙፋን ፊትብ ቀኝና በግራ ቁሞ ሁሉም እንደየሥራው ፍርድ መቀበሉን አትዘንጉ» ተብሎ ተወስኖአል ። (ፍትሐ ነገ - አንቀጽ ፳፪) ።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ለምእመናን የምታስተምረውና የምታስተላልፈው መልእክት ይኸው ከዚህ በላይ የተገለጸው ነው ። ለሞተ ሰው ማልቀስ የሚገባ ፣

፩/ ነፍሱ ከሥጋው በምትለይበት ጊዜ
፪/ በድኑ ከኖረበት ቤቱ ወጥቶ ወደ መቃብር ሲሄድ
፫/ ግብአተ መሬት ሲፈጸም ብቻ ነው ።

ይህም ቢሆን ሙሾ እያወጡና እየዘለሉ ፣ ደረትን እየደቁ ፣ ራስን እየተላጩ ፣ አካልን እያቆሰሉ ሳይሆን በትዕግስትና በመጠን መፈጸም ያለበት ነው ። ከዚህ የወጣው ኀዘንና ልቅሶ ሁሉ የተከለከለና የተወገዘ ነው ። ኀዘንተኞችም ይህን ሥርዓት ተላልፈው ቢገኙ ውግዘቱን መተላለፋቸው ሕገ እግዚአብሔርንም ማፍረሳቸው ነውና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት መቀጣት እንደሚገባቸው በጥቅምት ወር ፲፱፻፶ ዓ/ም የወጣው አንደኛ ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ሲኖዶስ ወስኖአል ።

ይህ ሁሉ እንዳይፈጸም ቅዱሳት መጻሕፍት የሚከለክሉ ፣ ቤተ ክርስቲያንም አጥብቃ የምታስተምረው የውግዘት ቃልም የምታስተላልፈው ቋሚ ወገኖች ለሞቱ ዘመዶቻቸው መሪር ኀዘን በማዘን በጤንነታቸው ጉዳት እንዳይደርስ ለመርዳት ከመሆኑም በላይ ክርስቶስ የሙታን ሁሉ በኵር ሆኖ የተነሣለት የክርስቲያን ሞት በእግዚአብሔር ዘንድ ፣ ክቡር ዕረፍትና ከሚያልፈው ወደማያልፈው ፣ ከጊዜያዊው ወደ ዘለዓለማዊው ፣ ከሥጋዊው ወደ መንፈሳዊው ዓለም መሸጋገር ስለሆነ ነው ። (መዝ- ፻፲፭ ፡ ፲ ዮሐ - ፭ ፡ ፳፬)

ይልቁንስ ማዘን ማልቀስ የሚገባ የራስን ኃጢአት የወገንን በደል ፣ ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን ግፍአ ሰማዕታትን እያሰቡ መሆን እንደሚገባ በጌታችን የተሰጠውን ትምህርት ማስተዋል ያስፈልጋል ። « - - - እናንተ የኢየሩሳሌም ልጆች (ደናግል) ለእኔ አታልቅሱልኝ - - - - ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ »የተባለው ለክርስቲያን ሁሉ መመሪያ ሊሆን ይገባዋል ። (ሉቃ - ፳፫ ፡ ፳፱) ስለራስ ኃጢአት ማልቀስም እንደአባታችን አዳም ፣ እንደ ቅዱስ ዳዊትና እንደቅዱስ ጴጥሮስ ነው ። (፪ ሳሙ ፲፪ ፡ ፲፮ ። ማቴ - ፳፮ ፡ ፸፭)

## ጸሎተ ፍትሐት

ቤተ ክርስቲያን ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ ታዝዛለች ። ፍትሐት ማለት ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩት ሰዎች በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ከሠሩት ኃጢአትና ከፈጸሙት በደል እንዲነጹ ወይም ከማዕሠረ ኃጢአት እንዲፈቱ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ጸሎት ማለት ነው ።

ጸሎተ ፍትሐት ለበደሉት ስርየተ ኃጢአትን ይቅርታን ዕረፍተ ነፍስን ያስጠል ። ለደጋጎቹ ክብርን የተድላ ዕረፍትን ያስገኛል ።

ሙታንና ሕያዋን የሚገናኙት በጸሎት አማካኝነት ነው ። «ሕያዋን ለሙታን ይጸልያሉ፤ ሙታንም ለሕያዋን ይለምናሉ»(ሄኖክ ፲፱፡፴፩) (ሕያዋን ለሙታን የሚጸልዩት ጸሎትና የሚያቀርቡት መሥዋዕት በግልጽ እንደሚታይ ሁሉ ሙታንም በአፀደ ነፍስ ሆነው በዚህ ዓለም ለሚቆዩ ወገኖቻቸው ሕይወትና ደኅንነት ስርየተ ኃጢአትንና ተስፋ መንግሥት ሰማያትን ጽንዓ ሃይማኖትንም እንዲሰጣቸው በንስሐ ሳይመለሱ ፣ ከብልየተ ኀጢአት ሳይታደሱ እንዳይሞቱ ፈጣሪያቸውን ይለምናሉ ። ይህም ሥርዓት እስከ ዕለተ ምጽአት ሲፈጸም የሚኖር ነው ።

ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ ፣ መሥዋዕት እንዲቀርብላቸው፣ በቤተ ክርስቲያንና በመካነ መቃብራቸው እንዲጸለይላቸው ቅዱሳን ሐዋርያት በዲድስቅልያ (ቀኖና ሐዋርያት) አዝዘዋል ። «በክርስቶስ አምነው ስለ ሞቱ ወንድሞቻችሁ ፣ ክርስቲያኖችና ሰማዕታት በቤተ ክርስቲያን ያለ ሐኬት ተሰብሰቡ ፣ በቤተ ክርስቲያን መሥዋዕት ሠውላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያንና ወደ መቃብር ስትወስዱአቸውም መዝሙረ ዳዊት ድገሙላቸው» ( ዲድስቅልያ አንቀጽ ፴፫ ፡ ገጽ ፩፻፹፩)

ነቢዩ ዳዊትም « የጻድቅ ሞቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ክቡር ነው ፤ ነፍሴ ሆይ ወደ ዕረፍትሽ ተመለሽ እግዚአብሔር ረድቶሻልና ፤ ነፍሴን ከሞት አድኖአታልና » በማለት ሙታን በጸሎት በምስጋና በመሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር እንዲሸኙ በመዝሙሩ ተናግሮአል ። (መዝ ፡ ፩፻፲፭-፯ መዝ - ፩፻፲፬ ፡ ፯ )

የቤተ ክርስቲያን የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ፍትሐ ነገሥትም በፍትሕ መንፈሳዊ በዲድስቅልያ የተጠቀሰውን ያጸናል (አንቀጽ ፳፪) ስለሙታን በሚጸለየው መጽሐፈ ግንዘትም ካህናት ለሞቱ ሰዎች ሊጸልዩ ላቸው ፣ በመሥዋዕትና በቁርባን ሊያስቧቸው ይገባል ። ካህናት ጸሎተ ፍትሐት በሚያደርጉላቸው ፣ መሥዋዕትና ቍርባን ስለእነርሱ በሚያቀርቡላቸው ጊዜ መላእክት ፣ ነፍሳቸውን ለመቀበል ይወርዳሉና ። ኃጢአተኞች ከሆኑ ስለ ስርየተ ኃጢአት ይለምኑላቸው ። ይማልዱላቸውዋል። ንጹሐንም ከሆኑ ደስ ይላቸዋል ። «ሰውን ለወደደው ለእግዚአብሔር በሰማያት ክብር ምስጋና ይገባል ፤ በምድርም ሰላም» እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ። ይህም የመላእክት ምስጋናና ደስታ ስለ ሰው ልጅ ደኅንነት ነው ተብሎ ተጽፎአል ።

የጻድቃን ሰዎችን ነፍሳት ቅዱሳን መላእክት እንደሚቀበሏቸው በቅዱስ ወንጌል ተጽፎአል «አልዓዛርም ሞተ ፡ መላእክትም ወደ አብርሃም ዕቅፍ ወሰዱት» (ሉቃ - ፲፮ ፡ ፳፪ ) ።

በዚሁ መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ለሞቱ ሰዎች ከጸአተ ነፍስ እስከ ርደተ መቃብር ፣ ከቤት እስከ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን ጸሎት ትጸልያለች መዝሙረ ስብሐት ታደርሳለች ።

## የሙታን አሸኛኘት ሥርዓት

ለሙታን ከሚደረገው ጸሎተ ፍትሐት ጋር ከጸአተ ነፍስ እስከ ርደተ መቃብር በቅደም ተከተል የሚፈጸሙ ሥርዓቶች አሉ ።

የክርስቲያኖች ዕረፍት ክቡር ነው ። በመሆኑም የአሸኛኘቱ ሥርዓት የራሱ የሆነ ወግ ማዕርግ አለው ። የሟች ቤተሰብ ወዳጅ ዘመድና የቅርብ ጎረቤት ካህናትና ምእመናን ይሰበሰባሉ ። ካህናት በመዝሙር ፣ በማሕሌትና በይባቤ ሕዝቡ በኀዘን በልቅሶና በእንባ ይሸኙታል ። ይህም አይነት የአሸኛኘት ሥርዓት በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቦ የሚገኝ ነው ። «ዮሴፍም አባቱን ሊቀብር ወጣ ፣ የፈርኦንም ሎሌዎች ሁሉ ከእርሱ ጋር

ወጡ ። የቤቱ ሽማግሌዎችም የግብፅ ምድር ሽማግሌዎችም ሁሉ የዮሴፍ ቤተሰቦች ወንድሞች የአባቱ ቤተሰቦች ሁሉ ወጡ ። ልጆቻቸውንና በጎቻቸውን ከብቶቻቸው ንም በጌሤም ምድር ብቻ ተው ። ሠረገሎችም ፈረሰኞችም ከእርሱ ጋር ወጡ ሠራዊቱም እጅግ ብዙ ነበሩ እጅግ ታላቅ በሆነ በጽኑ ልቅሶ አለቀሱለት - - - በዚያች ምድር የሚኖሩ የከነዓን ሰዎችም የሆነውን ልቅሶ ባዩ ጊዜ - - - ይህ ለግብጽ ሰዎች ታላቅ ልቅሶ ነው አሉ» (ዘፍ - ፶ ፣ ፯—፲፩) ። ንጉሡ ሕዝቅያስም ከአባቶቹ ጋር በሞት (በአንቀላፋ ጊዜ) ልጆቹ ቤተሰቦቹና የኢየሩሳሌም ሰዎች ሁሉ በሞቱ እንዳከበሩት ተጽፎአል (፪ዜና ፣ ፴፪ ፣ ፴፫) ።

የሟቹ በድን ከቤት ወደ ቤተ ክርስቲያን እስከሚደርስ እንደ አስፈላጊነቱ በሰባት ምዕራፎች የተከፈለ የገንዘ ፍትሐት ይደረግለታል ። በድን ከቤተ ክርስቲያን ሲደርስም በደጀ ሰላም አርፎ ጸሎት ይደረግለታል ።

የሙታንን አስከሬን እስከ ወሪደ መቃብር ባለው ጊዜ በቤትም ሆነ በቤተክርስቲያን በተለየ ቦታ ማቆየት በቅዱሳት መጻሕፍትና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ነው ።

«ሱናማዊቷ ሴትዮ ልጅዋ በሞተባት ጊዜ ነቢየ እግዚአብሔር ኤልሳዕ መኝቶ እስኪያስነሣላት ድረስ ነቢዩ ኤልሳዕ ያርፍበት በነበረው ክፍል ለይታ አቆይታዋለች» ።(፪ ነገሥ፡ ፬ ፣ ፳፩ ) አሳ የተባለውም ንጉሥ በሞት ጊዜ በዚሁ ልማድ በተለየ ቦታ እንዳቆዩት ተጽፎአል ። (፪ ዜና፡ ፲፮ ፡፩) በሐዲስ ኪዳንም ጣቢታ (ዶርቃ) የተባለችው ሴት በሞተች ጊዜ አጥበው በሰገነት በተለየ ቦታ እንዳቈዩአት በሐዋርያት ሥራ (፱ ፣ ፴፮ ፴፯) ተጽፎአል ።

በዚሁ ትውፊት መሠረት የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት የሆኑ ሁሉ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በቤተ ክርስቲያን የጸሎት ሥርዓት ይፈጸምላቸዋል ። አስከሬን በቤተ ክርስቲያን ማሳደር ግን የተከለከለ ነው ።

## የሥጋብት ሥርዓት (ሰዒም)

በዚህ ዓለም በሚኖሩ ሰዎች ባህልና ልማድ በመገናኛት ጊዜ ናፍቆት ፍቅር ፣ አክብሮትና መሳሳም እንዳለ ሁሉ በመለያየትና በስንብት ጊዜም ተመሳሳይ ሁኔታ ይፈጸማል ። በዚህ ዓለም ሩቅ መንገድ የሚሄድ ሰው ውሎ አድሮ ይመለሳል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል ። ያም ሆኖ ሲሄድም ሲመለስም በመሳም ይሸኙታል ፣ ይቀበሉታል ። እንደዚሁም ሰው በሚሞትበት ጊዜ ናፍቆቱ ፣ ትዝታው ፣ ፍቅሩ የተለየ ስለሆነ አጥበን ገንዘን ፣ ሽቱ አርከፍክፈን ስመን በኀዘንና በልቅሶ እንሸኘዋለን ። በትንሣኤ ዘጉባኤ እንደሚነሣ በማመን «ግብኢ ነፍስየ ውስተ ዕረፍትኪ» እያልን በመዝሙርና በምስጋና እንሰናበተዋለን ።

ለሙታን የተመደበው ሥርዓት ጸሎት ከተፈጸመ በኋላ በመሳም ይሰናበቱታል ። ይህም ከቅዱሳት መጻሕፍት የተገኘና በሥርዓት ቤተ ክርስቲያን የተደነገገ ነው ።

«ያዕቆብም ትዛዜውን ለልጆቹ ተናግሮ በፈጸመ ጊዜ እግሮቹን በአልጋ ላይ ሰብስቦ ሞተ ፤ ወደ ወገኖቹም ተከማቸ ። ዮሴፍም በአባቱ ፊት ወደቀ ፤ በርሱም ላይ አለቀሰ ፣ ሳመውም» (ዘፍጥ ፣ ፵፱ ፣ ፴፫ ። ፶ ፣ ፩) ። እንደዚሁም በፍትሐ ነገሥት በፍትሕ መንፈሳዊ «የሞተውን ስመው ይሰናበቱት» ተብሎ ታዝዞአል ። (አንቀ - ፳፪) በመጽሐፈ ግንዘትም ይኸው ድንጋጌ ተጽፎአል ።

ከዚህ በኋላ በድኑ በጸሎትና በስብሐተ እግዚአብሔር ዑደት አድርጎ ወንድ ከሆነ በወንዶች በር ራሱን ወደ ቤተ መቅደስ መልሰው ያስግዱታል ። ሴት ከሆነችም በሴቶች በር ራስዋን ወደ ቤተ መቅደስ መልሰው ያሰግዱዋታል ።(ትሰግዳለች) ይህም ሥርዓት ከቅዱሳት መጻሕፍት የተገኘ እንጂ በልማድ የሚፈጸም አይደለም ። የሟች ነፍስ በዐፀደ ነፍስ ለፈጣሪዋ እንደምትሰግድ ሁሉ በድኑ በዐፀደ ሥጋ በቤተ ክርስቲያን እንዲሰግድ የሚደረገው በዚህ አንጻር ነው ። « የሞትስ ነገር እንደዚህ ነው ፤ ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ የትእዛዝ ቃል ከመጣ በኋላ አንሌ ይሙት ባለጊዜ ነፍሱ ከሥጋው ትለያለች ወደሰጭዋ ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለች ፤ ለጌትነቱም አስቀድማ ትሰግዳለች ። (ዕዝ ፡ ሱቱ ፡ ፯ ፡ ፴)

ሥርዓተ ዑደትም አንጻራዊ ትርጉም አለው ። ሱቱኤል ዕዝራና ሄኖክ ፣ እንዲሁም ወንጌላዊ ዮሐንስ በራእይ እንዳዩት ቅዱሳን መላእክት ለሙታን ነፍሳት ዓለመ መላእክትን መካነ ነፍሳትን እያዞሩ ያሳዩአቸዋል። በዚህ አንጻር ለሟቹ በድን በአጸደ ሥጋ በቤተክርስቲያን ዑደት ይደረግለታል ። ይህንም በሱቱኤል ዕዝራና በሄኖክ መጻሕፍት በሰፊው መመልከት ይቻላል ።

## ሥርዓተ ቀብር

ከዚህ በላይ በዝርዝር የተገለጠው ያሸኛኘት ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ መጨረሻው ወረደ መቃብር ነው ። በድኑ በተዘጋጀው መካነ መቃብር ካረፈ በኋላ የመጨረሻው ሥርዓተ ጸሎት ይፈጸምለታል ። ካህን የሆነ እንደሆነ በሥርዓተ ግንዘቱ ጊዜ እንደ ተፈጸመው መብራቶች ይበራሉ ማዕጠንት ይደረጋል ፣ መቃብሩ ይባረካል ። «አሐዱ አብ ቅዱስ ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ» ተብሎ ይጸለያል ። ሕዝባዊ የሆነ እንደሆነ የመብራቱና የማዕጠንቱ ሥርዓት እንዳለ ሆኖ መቃብሩ ይባረካል ፤ ፍትሐት ዘወልድ ይጸለያል ። ይህም የፍትሐት ዘወልድ ጸሎት ለሁሉም የሚፈጸም ነው ።

በመጨረሻም በሥርዓተ ቀብሩ ላይ የተገኙት ካህናት ሁሉ ከመካነ መቃብሩ አፈር ዘግነው በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ «ሰው ሆይ መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ» እያሉ አፈሩን ሕራረ ፣ ዕጣኑን ወይም ሕሙቱን በአስከሬን ላይ ይበትኑታል ። ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ በበድኑ ላይ አፈር በመመለስ መቃብሩ ተሞልቶ ጠቅላላ የቀብሩ ስነ ሥርዓት በዚሁ ይፈጸማል ።

## ከቀብር መልስ እጅን የመታጠብ ልማድ

ከቀብር መልስ እጅን መታጠብን በተመለከተ በብሉይ ኪዳን የተጻፈው የሞተውን ሰው በድን ወይም መቃብሩን የሚነካ ፣ እንደ ርኩሰት ስለሚቈጠርበት እስከ ሰባት ቀናት ሁለንተናውን መታጠብ እንዳለበት ይገልጣል ። ይህም ይደረግ የነበረው ከርኵሰት ለመንጻት ነው ።

ይሁን እንጂ የክርስቲያኖች አካል በጥምቀተ ክርስትና የነጻ ፣ በክርስቶስ ሥጋና ደም የከበረ ስለሆነ ከቀብር መልስ የሚፈጸመው ሕጽበት በኦሪቱ እንደተመለከተው አይደለም ። በሥርዓተ ቀብር ጊዜ በድን አጥበው የሚገንዙ ፣ መቃብር የሚምሱ ፣ አፈር የሚመልሱ ፣ ዕንባቸውን የሚያብሱ ስላሉ ፣ ወዲያውም ወደ ቤት በመግባት የእዝን እንጀራና ዕንባ አድርቆ መመገብ ስላለ ተገቢውን ንጽሕና ለመጠበቅ ሲባል የሚደረግ ነው ።

# የእዝን እንጀራ

በኢትዮጵያውያን ልማድና ባህል ሰው ሲሞት ከጸአተ ነፍስ እስከ ወረደ መቃብር የሟች ቤተሰብ እህል ውሃ አይቀምስም ። በገጠሩ ነዋሪ ሕዝብ ዘንድ በቆየው ልማድና ሥርዓትም አንድ ሰው ሲሞት ባደጋና በቈላ ፥ በሩቅና በቅርብ ያለው ዘመድ ሁሉ ተጠርቶ እስከሚሰበሰብ ሥር ዓት ቀብሩ እንደ የአካባቢው ሁኔታ ውሎ የሚያድርበት ጊዜ አለ ። በዚህም ምክንያት ኀዘንተኞች እህል ውሃ ሳይቀምሱ ውለው ስለሚያ ድሩ ሰውነታቸው ይጎዳል ። ንጉሥ ዳዊት ወዳጁ አበኔር በሞተ ጊዜ ይህን ሥርዓት ፈጽሞታል ።« ሕዝቡም ሁሉ ገና ሳይመሽ ዳዊትን እንጀራ ይበላ ዘንድ ሊጋብዙት መጡ ዳዊት ግን ፀሐይ ሳትጠልቅ እንጀራ ወይም ሌላ ነገር አልቀምስም ብሎ ማለ ። ሕዝቡም ሁሉ ይህን ተመለከቱ፡ ደስ አሰኛቸውም ። በሕዝቡም ሁሉ ፊት ንጉሥ ያደረገው ሁሉ ደስ አሰኛ ቸው» (፪ ሳሙ ፣ ፫ ፣ ፴፭)

ጌታችን በሞተ ጊዜ ሐዋርያት መነሣቱን ሳናይ አንመገብም በማለት አክፍለዋል ።

በመሆኑም ኀዘንተኞችን ለማረጋጋት ከኀዘናቸው ለማጽናናት ና ከድ ካማቸው ለማበርታት የእዝን እህል ውሃ (እንባ አድርቅ) ወደ ቤተ ክርስ ቲያን እንዲሄድ ይደረጋል ። ለጸሎተ ፍትሐትና ለልቅሶ የተሰበሰበው ካህንና ሕዝብም ወደ ኀዘኑ ቤት ሳይመለስ ወደየመጣበት ስለሚሄድ የእዝኑ እንጀራና ንፍሮ በደጀ ሰላምና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ በየመዐ ዝኑ እንዲቀመስ ይደረጋል ።

ከቅርብ ጎረቤት ፥ ከዘመድና ከወዳጅ የሚመጣው የእዝን እህል ውሃ ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ የነበረና ያለ ነው ። በጥንቱ ጊዜ ኀዘን ተኞችን ኀዘናቸውን ለማስተው ሕይወታቸውን ለማረጋጋትና ለማጽ ናናት ጥቂት ጽዋ ወይንና የበሰለ እህል የማቅረብ ልማድ ነበር (ኤር ፣ ፲፮ ፣ ፯ ። ሆሴ ፣ ፱ ፣ ፬)

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈጸመው ሥርዓተ ኀዘን በአብዛኛው ተመ ሳሳይ ቢሆንም በአንዳንድ ክፍሎች ከጥንት ጀምሮ የተወረሱት እንደተ ጠበቁ ሲገኙ በሌሎች ደግሞ ከጥንቱ የቀሩ ፣ አዲስ ሆነው የሚታዩ ይኖ ራሉ ። በክርስቲያኖች ሞት ሥርዓት ቅዳሴ ስለሚከናወን (መሥዋዕት ስለሚቀርብ ) የመገበሪያ እህልና አስፈላጊው መባዕ ይቀርባል ። ጠበልና ጠዲቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይወሰዳል ። ይህም በጸሎተ ፍትሐት ያገለገሉ ካህናት ከቅዳሴ በኋላ አፍ የሚያድሩበትና ለነዳያን የሚሰጥ ምጽዋት ነው ። ለሟችም መታሰቢያ ነው ።

# በመካነ መቃብር ላይ አበባ ማኖር

እንደ ሐውልትና የመቃብር ቤት ሕንጻ ሁሉ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እየተስፋፉ ካሉት እንግዳ ሥርዓቶች ውስጥ ጥቂቶች በመካነ መቃብር ላይ የአበባ ጉንጉን ማስቀመጥ፥ ጥቁር ልብስ መልበስን የመሳ ሰሉ ናቸው ።

ይህ ልማድ በኢትዮጵያ ሀገራችን የተጀመረበት ጊዜ በትክክል ባይታወቅም ከውጭው ዓለም የተገኘ ፣ የተውሶ ባህልና እንግዳ ሥርዓት መሆኑ አያጠያይቅም ። በሀገራችን መሠረትም ትውፊትም የለውም ። በሀገራችን የቆየውና የታወቀው ሰው ሲሞትና ለቀብር ወደ ቤተ ክርስቲ ያን ሲወሰድ አብሮ የሚሄደው ጥቂት ምግብና መጠጥ ነው ። ይህም ልማድ “ እናንተ የኢትዮጵያ ሰዎች ወገናችሁ ሲሞት ወደ ቤተ

ክርስቲያን ምግብ ትወስዳላችሁ ለመሆኑ ሟቹ ዘመዳችሁ መቼ ነው የሚመገበው ? ለተባለው ጥያቄ የናንተ ሰው ተነሥቶ በመቃብር ላይ የተቀመጠለትን አበባ በሚያሸትበት ጊዜ ነው፡ ”ተብሎ የተገለጸው መልስ አበባ በመካነ መቃብር ላይ ማስቀመጥ ኢትዮጵያዊ ትውፊት የሌለው መሆኑን ያረጋግጣል ።

በተለያዩ ኅብረቀለማት አሸብርቀው ፣ ከተለያዩ ዕፀዋት የሚገኙ አበቦች በቀለማቸውና በመዓዛቸው ሕይወትን ደስ ያሰኛሉ ። ዕፀዋት ከባሕርያቸው የሚያስገኙአቸው አበቦች ያላቸው ውበትና መዓዛ እን ሰሎሞንን የመሰሉ ታላላቅ ጠበብትና ነገሥታት እንኳ ባላቸው ክብርና ጌትነት ሊያገኙትና ሊጎናጸፉበት ያልቻሉ መሆኑን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮላቸዋል ። (ማቴ፮፡ ፳፰—፳፱)

ይሁን እንጂ የአበባ ዕድሜ ረጅም አይደለም ፣ ቶሎ የሚጠወልግ የሚደርቅና የሚረግፍ ታይቶ የሚጠፋ ነው ። የሰው ዘመንም እንደዚሁ ትንሽ ስለሆነ ዕድሜው እንደ አበባው ክብሩም እንደሚረግፈው የሣር ፍሬ መሆኑ ተጽፎአል ። አበባው በመካነ መቃብር የሚቀመጠው በዚህ መልኩ ነው ፤

“ሰውስ ዘመኑ እንደሣር ነው ፤ እንደዱር አበባ
እንዲሁ ያብባል ፣ ነፋስ በነፈሰበት ጊዜ ያልፋል ፤
ሥፍራውንም ደግሞ አያውቅም ፤ ያ ፈጥኖ ደርቆ እንዲጠፋ
ሰውም እንደዚሁ ይጠፋል ያልፋል ፤ ነፍሱ ከሥጋው ከተለየች
በኋላ አይመለስም” (መዝ ፡ ፻፪ ፡ ፲፭—፲፮) ተብሎ እንደተጻፈ የሰውን ታይቶ መጥፋት በማሰብና በማስተዋል ከሆነ ትርጉም ሊኖረው ይችላል ። ይህም ቢሆን ሰው እንደሣር እንደ አበባ ረግፎ ሳይቀር በትንሣኤ ዘጉባኤ ክርስቶስን መስሎ የሚነሣ ስለሆነ በቀቢጸ ተስፋ ሕይወቱ ከንቱ ሆኖ መታሰብ የለበትም ።

ጻድቁ ኢዮብም “ከሴት የተወለደ ሰው የሕይወቱ ዘመን ጥቂት ነው ። መከራም ይሞላዋል እንደ አበባ ይወጣል ፣ ይጠወልጋል ፣ ይረግፋል ፤ እንደጥላም ይሸሻል ፣ እሱም አይኖርም” በማለት ሰው በሥጋ ሕይወት የሚኖረው ዘመን ከአበቦች አንፃር የሚታይ መሆኑን አመልክቷል ኢዮ ፡ ፲፬ ፡ ፩ ።

ሆኖም በሞተ ሥጋ ከዚህ ዓለም ቢለይ ፣ ዘመኑም እንደ አበባ ጥቂት ቢሆን ትንሣኤ ሙታን መኖሩን ረጅሙንና መጨረሻ የሌለውን ዕድሜ መኖር የሚቻለውም ከትንሣኤ በኋላ ባለው ሕይወት መሆኑን በመግለጽ

“እኔ ግን የሚቤዠኝን ሕያው እንደሆነ በመጨረሻ ዘመን
በምድር ላይ እንዲቆም ፤ ይህ ሥጋየም ከጠፋ በኋላ
በዚያን ጊዜ ከሥጋየ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ
አውቃለሁ ፤ እኔ ራሴ አየዋለሁ ፤
ዐይኖቼም ይመለከቱታል ፤ ··· ልቤ በመናፈቅ
ዝሎአል ” በማለት ጽፎአል ። (ኢዮ ፡ ፲፱ ፡ ፳፭-፳፯) ።

ስለሆነም አበባ በመካነ መቃብር ላይ መቀመጡ ለሟች የሚሰጠው ምንም ጥቅም ካለመኖሩም በላይ ፣ ሟችን በመቃብር ጥለነው ተመለስን ብሎ የሞተውን ወገናችንን በሚያልፍና በሚጠፋ አበባ ሕይወት አንፃር በቀቢፀ ተስፋ ማሰብ ስለሌለብን ጥንትም የኛ ያልነበረ በመኖሩም የማይጠቅመውን ይህን የተውሶ ልማድ መተው ይበጃል ። በዚያ ፈንታ ይልቅ ለአበባ ጉንጉን የሚወጣው ገንዘብ ለተቸገሩ ወገኖች ቢሰጥ ወይም የሟች ቤተሰብ ቢረዳበት ጠቀሜታ አለው ። ከዚህም ጋር መካነ መቃብርን

ውለው አድረው የጤና ጠንቅ በሚፈጥሩ ነገሮች ከማበላሸት ፣ ቤተ ክርስቲያን በአጸድ ዛፎች እንድታጌጥ ፣ የመቃብር ሥፍራዎች ልዩ ልዩ ኅብረ መልክዕ ባላቸው አትክልቶችና አበቦች ተውበው ከመቃብር ባሻገር የሚጠበቀው የትንሣኤ ተስፋ የሚታይባቸው የልምላሜ ሥፍራዎች እንዲሆኑ ሰዎች በዕረፍትና በጸሎት ጊዜአቸው በሚመላለሱበት ጊዜ ዐይኖቻቸው መልካም ነገሮችን በማየት ደስ ሊሰኙ የሚችሉባቸው ሆነው ቢዘጋጁ እጅግ መልካም ነው ። ቤተ ክርስቲያን የክርስቲያኖች ሁሉ አምልኮት መፈጸሚያ ፣ መሥዋዕትና ጸሎት ማቅረቢያ እንደመሆኗ ጌታ ለጸሎት ቦታ የመረጣት የአትክልትና የአበቦች ሥፍራ የሆነች የጌተሴማኒ አምሳል መሆን ይኖርባታል ። የጸሎት ቦታና የመካነ መቃብር ምሳሌ ጌቴሴማኒ ብቻ ሳትሆን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የተቀበረው ልምላሜና ውበት ባላት በአትክልት ሥፍራ ነበር ። (ማቴ ፳፮ ፥ ፴፮ ፤ ዮሐ ፲፱ ፥ ፵፩)

እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ነው ። ንጹሕ ነገርን ይወዳል ። ቅዱስ ነው ። እኛም እንደሱ ቅዱሳን እንድንሆን አዟል ። ንጹሕና ቅዱስ የሆነው የባሕርይ አምላክ የሚመሰገንባት ቤተ ክርስቲያንም በሁለን ተናዋ ንጽሕት ፣ ቅድስት ፍጹም የሕይወት ተስፋ የሚታይባት የክርስቲያኖች ቤት (መካነ ዕረፍት) መሆን ይኖርባታል ።

## የኀዘን ልብስ

ሰው በሞተ ጊዜ የሟች ቤተሰቦችና የቅርብ ዘመዶች በተለያየ ቀለም የተነከረ ጥቁር (ከል የገባ) ልብስ መልበስ ፣ ነጠላን አዘቅዝቆ ማሸረጥ ፣ በርኖስ መገልበጥ በዘመናችንም ፎጣ መደረብ የጥቁር ጨርቅ እራፊ በልብስ ላይ መለጠፍ ፀጉርን ተላጭቶ ጥቁር ኮፍያ ማድረግ ጺምን ማሳደግ በገጠሩም የሟችን ልብሶች እየያዙ ማልቀስ የተለመደ ሆኗል ።

ይህ ልማድ የሚጎዳ እንጂ የሚጠቅም አይደለም ። ሐዋርያዊ ትውፊትና ቀኖናዊ ሥርዓትም አይደለም ። ከዚህም ጋር ከል ወይም አጥላስ (የኀዘን ልብስ) ዘወትር የማይለበስ ከመሆኑም በላይ በሟች ቤተሰቦች ላይ የኢኮኖሚ ችግርን መፍጠሩ አልቀረም ።

እነዚህ ልዩ ልዩ ኬሚካል ባላቸው ቀለሞች የሚነከሩ ጥቁር ልብሶችና የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ በጤናም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርሱ የታወቀ ነው ።

በመሠረቱ የሞተ ሰውን በጥቁር ጨርቅ ሳይሆን በነጭ ልብስ መገነዝ ተስፋ ትንሣኤን ለማብሰር ከመሆኑም ጋር ስለ ሞተ ሰው ጥቁር ልብስን መልበስ እንደማይገባ ያሳያል ። ነቢዩ ዳዊት ልጁ በታመመ ጊዜ የኀዘን ልብስ ለብሶ አዘኖ ፣ ሕፃኑ ከሞተ በኋላ ግን የኀዘን ልብሱን ለውጦ ልብሰ መንግሥቱን ለበሰ ፣ (፪ ሳሙ ፲፪ ፥ ፳ ። ) መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከሙታን ተለይቶ በተነሣ ጊዜ መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው በጌታችን ሞት አዝነው የነበሩ ቅዱሳት አንስትን "አትፍሩ" በማለት አጽናንተዋቸዋል ። (ማቴ ፳፰ ፥ ፩-፯) በዓርባኛውም ቀን ባረገ ጊዜ መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው በመታየት "እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል" በማለት ሐዋርያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተለያቸው እንዳያዝኑ ነግረዋቸዋል (የሐዋ ፩ ፥ ፱—፲፩) ይህን መሠረት በማድረግ ቤተ ክርስቲያናችን ስለሞቱ ሰዎች የኀዘን መግለጫ የሚለበሰውን ጥቁር ልብስና የሚደረጉትን ልዩ ልዩ ምልክቶች ሁሉ ትከለክላለች ።

ይህን በተመለከተ በሀገራችን ደቡባዊ ክፍል በተለይም በጉራጌ ኅብረተሰብእ በዕድሜ የበለጸጉ ሰዎች ሲሞቱ በሕይወታቸው ቤተሰባቸውና ዘመድ አዝማድ ያደረገላቸውን እንክብካቤ በማስታወስ ለቋሚዎች ቤተሰቦቻቸው በሚያደርጉት ኑዛዜ ምርቃታቸውን በረከታቸውን ያስተላልፋሉ።በሚሞቱበትም ጊዜ በሞታቸው ምክንያት ጠጉርን በመላጨት ደረትን በመግለጥና በመምታት ፊትን በመንጨት ጥቁር እንዳይለብሱና መሪር ኀዘን እንዳያዝኑ የአደራ ቃላቸውን ያስተላልፋሉ ። ይህም በቋሚ ወገኖቻቸውም ዘንድ ተግባራዊ ሆኖ ስለሚታይ ቤተ ክርስቲያን በመልካም አርአያነታቸው ታመሰግናቸዋለች፤ሌላውም ክፍል ይህን ምሳሌ እንዲከተል ታስገነዝባለች ።

## ዐውደ ቤተ ክርስቲያን (ማርገጃ)

ከቤተ ክርስቲያን በስተምዕራብ ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውጭ የሚገኘው ዐደባባይ "ማርገጃ" ይባላል ። ይህም ሰፋ ብሎ የሚገኘው ቦታ ወደ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ለመግባት የማያስችል ምክንያት ያላቸው ምእመናን ቆመው የሚያስቀድሱበትና የሚጸልዩበት ፤

- በታላላቅ የበዓላት ቀኖች ታቦታት ወጥተው ሥርዓተ ንግሥ የሚፈጸምበት ፤
- ሰው በሞተ ጊዜ ከቤቱ ቤተ ክርስቲያን እስከሚደርስ ከሚደረገው የጉዞ ጸሎተ ፍትሐት የመጨረሻው የሚከናወንበት ምዕራፍ ፤
- ኀዘንተኞች በክርስቲያናዊ ሥርዓት ለሚች የተወሰነ ልቅሶ የሚያደርጉበትና ከቀብር መልስ ለኀዘን የተሰበሰበውን ሕዝብ የሚያሰናብቱበት ቦታ ነው ። ማርገጃ ስሙ እንደሚያመለክተው በልማድና ከሥርዓት ውጪ በሆነ መንገድ ሙሾና ረገዳ የሚደረግበት አይደለም ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባህልና ሥርዓት በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከቅጽር ውስጥና ውጭ የሚገኙ ቦታዎች ከላይ እንደተጠቀሰው ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጥባቸው ናቸው ። ያለ አገልግሎት የሚኖር ክፍት ቦታ የለም ። አካባቢውም የተቀደሰ ነው ። ንብረቶችም ሁሉ የተጠበቁና የተከበሩ ናቸው ከአንዲት የአጸድ ዛፍ ደርቃ የምትወድቅ እንጨት እንኳ አትነካም ይህም በገጠሩ እስከዛሬ በአብዛኛው ክፍል የተጠበቀ ነው ።

ነገር ግን በከተሞች በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ለተለየ መንፈሳዊ አገልግሎት የተወሰነው ማርገጃ (ዐውደ ቤተ ክርስቲያን) አንዳንድ ጊዜም የቤተ ክርስቲያኑ መግቢያና መውጫ የውስጥ ዐውደ ምሕረትም እስከሚጠብ የደራ ገበያ ማካሄጃ፤የግለሰቦች መኪና ማጠቢያ የተለያዩ ሰዎች መጠለያና በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሊታይ የማይገባው አልባሌ የጤና ጠንቅ ማከማቻ ሆኖ መታየቱ እጅግ የሚያሳዝንና የሚያሰቅቅ ነው ። ይህም ፍጹም የቁጥጥር አለመኖርና የባለቤትነት መንፈስ ከእያንዳንዱ ማንነት ያሳያል ።

ስለዚህም የሰበካው ምእመናን የደብሩ ካህናትና የአካባቢው ክርስቲያን በቅንጥጥሩ ሊተባበሩበትና ዘላቂ መፍትሔ ሊፈልጉለት ይገባል ።

# ሐውልት

ሐውልት አንድ ወጥ የሆነ ክብነት ወይም ማዕዘንነት ያለው በድን ጊያ ተጠርቦ ከኖራና ከአሸዋ ፣ ከሲሚንቶና ከተፈጨ ደንጊያ ተሠርቶ ለመታሰቢያ የሚተከል ፣ እንደ ዐምድ (እንደ ምሰሶ) የሚቆም መዘክር ነው ። የሚያመለክተው በአንድ ዘመን አንድ ቦታ ላይ የተፈጸመ ድርጊትን ስለሆነ ከብዙ የድንጋይ ቁልል (ጉር) ሊሠራ ይችላል ።

በቀድሞ ጊዜ ሐውልት የሚቆመው በጦር ሜዳ ወድቀው ለሚቀሩ ጀግኖች፤በስደትና በሽሽት ጊዜ በጉዞ ላይ በሚደርስ ድንገተኛ ሞት ከቤተሰብ ተለይተው በመንገድ ዳር ለሚቀበሩ ወገኖች መታሰቢያ ነበር ።

ሐውልት በመታሰቢያነት ብቻ ሳይሆን በሁለት አዋሳኝ አገሮች ወይም በሁለት የተለያዩ ሕዝቦች የመሬት ክልል ለድንበር፤ለወሰን የሚቆም ምልክትም ነው ። በሁለት ወገኖች መካከል በአንድ ጉዳይ ላይ በሚደረግ ስምምነት ለትውልድ ማስታወሻ ወይም ለቃልኪዳን ምልክት የሚቆም መታሰቢያም ይኖራል (ዘፍ ፡ ፴፩ ፡ ፵፭-፶፫ ፤ ፩ ሳሙ ፯ ፡ ፲፪)

ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው ሸሽቶ ወደ አጎቱ ወደላባ በሄደበት ጊዜ ፈጣሪው በመንገዱ ሁሉ ጠብቆ በሰላም እንዲመልሰው ለሕይወቱ አስፈላጊ በሆኑ ነገሮችም እንዲረዳው ብፅዓት በማድረግ አንድ ሌሊት ባሳለፈበት ሥፍራ ተንተርሶት የነበረውን ደንጊያ ሐውልት አድርጎ እንዳቆመው ተጽፎአል ። (ዘፍ ፡ ፳፰ ፡ ፲—፳፪)

እግዚአብሔር ሕዝበ እሥራኤልን በኢያሱ መሪነት የዮርዳኖስን ውኃ ከሁለት ከፍሎ በደረቅ ምድር ባሻገራቸው ጊዜ ኢያሱ በአሥራ ሁለቱ ነገደ እሥራኤል ልክ ከዮርዳኖስ ወንዝ የወሰዱአቸውን አሥራ ሁለት ድንጋዮች ለመታሰቢያ ሐውልት አድርጎ እንዳቆማቸው ተገልጾአል ።

"ኢያሱም ከየነገዱ አንዳንድ ሰው አድርጎ ያዘጋጃቸውንአሥራ ሁለት ሰዎች ጠራ ፣ እንዲህም አላቸው፣ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ወደ ዮርዳኖስ መካከል እለፉ ከእናንተም ሰው ሁሉ በእሥራኤል ልጆች ነገድ ቁጥር በትከሻው አንድ አንድ ድንጋይ ከዚያ ይሸከም ፤ ይህም በመካከላችሁ ምልክት ይሆናል ልጆቻችሁም በሚመጣው ዘመን የእነዚህ ድንጋዮች ነገር ምንድነው ? ብለው ሲጠይቋችሁ ፣ እናንተ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት የዮርዳኖስ ውኃ ስለተቋረጠ እነዚህም ድንጋዮች ለእሥራኤል ልጆች ለዘለዓለም መታሰቢያ ይሆናሉ ትሉአቸዋላችሁ» (ኢያ ፡ ፬ ፡ ፬-፯) መስፍኑ ኢያሱ ሕዝበ እሥራኤልን በሴኬም ሰብስቦ እግዚአብሔር ከአብርሃም እስከ ሙሴ በልዩ ልዩ መንገድ ያደረገውን ውለታ ባለመዘንጋት ከአምልኮቱ እንዳይወጡ ቃል ኪዳን በማስገባት ሐውልት አቁሟል ። (ኢያ ፡ ፳፬ ፡፳፮ ፡ ፳፯ )

ሐውልት አንዳንድ ጊዜም ላልወለዱ መካኖች በልጆች ፈንታ መታሰቢያ ሆኖ እንደሚቆም በቅዱስ መጽሐፍ የሚገኙ ታሪኮች አሉ ።

«አቤ ሴሎምም በሕይወቱ ሳለ ስለስሜ መታሰቢያ የሚሆን ልጅ የለኝም ፤ ብሎ ሐውልት ወስዶ በንጉሥ ሸለቆ ውስጥ ለራሱ አቁሞ ነበር ፤ ሐውልቱንም በስሙ ጠርቶት ነበር ። እስከ ዛሬም ድረስ የአቤሴሎም መታሰቢያ ተብሎ ይጠራል» (፪ ሳሙ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰) ።

ከዚህም ሌላ ሐውልት ለመልካም ሥራና ለደግ ነገር መታሰቢያ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ ውጭ በተፈጸሙ ሥራዎች ለደረሱ ቅጣትና ተግሣፅ ማስታወሻ ሆነው የቆሙ ሐውልቶችም አሉ ። እግዚአብሔር የሰዶምንና የገሞራን ሰዎች በኀጢአታቸው በመታቸውና ምድራቸውን በእሳትና ዲን ባቃጠለው ጊዜ ሎጥና ልጆቹ

በቸርነቱ ከመዓቱ ሲወጡ የሎጥ ሚስት ከእግዚአብሔር የተሰጠውን መመሪያ ባለመጠበቋ የጨው ሐውልት ሆና እንደ ቀረች መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ። (ዘፍ ፣ ፲፱ ፣ ፳፮)

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ጥቅሶችና ታሪኮች ሁሉ የሚገልጹት ሐውልት በሙታን መቃብር ላይ ብቻ የሚቆም የሙታን መታሰቢያ ሳይሆን ለልዩ ልዩ ታሪክና ሥራ ፤ ለቃል ኪዳንና ለወሰን መለያ የሚተከል ምልክት መሆኑን ነው ።

በመካነ መቃብር ላይ የመታሰቢያ ድንጋይ (ሐውልት) የማቆም ታሪክ የተጀመረው በነያዕቆብ ዘመን ነው ። ያዕቆብ በራሔል መቃብር ላይ የመታሰቢያ ሐውልት እንዳቆመ ተጽፎአል ። (ዘፍ ፣ ፴፭ ፣ ፳) ከታሪኩ መረዳት እንደሚቻለው አንድ ወጥ የሆነ የቆመ ድንጋይ ምልክት እንጂ ዛሬ በዘመናችን በተለያየ ቅርጽና መልክ እንደሚሠራው ያለ የጥርብ ድንጋይና የዕብነ በረድ ፤ የአሸዋና የሲሚንቶ ፣ የኖራና የጠጠር ክምር አይደለም፤ያዕቆብም ለራሔል የመታሰቢያ ሐውልት ያቆመበት ምክንያት ወደሀገሯ ሳትገባ በድንገት በመንገድ ዳር አርፋ ከወገኖቿ ጋር ለመቀበር ዕድል ሳታገኝ በመቅረቷ ነው ። ሐውልት በመታሰቢያ ነቱ ትውፊቱ አለ ። ስለሆነም አሠራሩም ሆነ አፈጻጸሙ በዘመናችን እንደሚታየው ያለ ሁኔታ አልነበረም፤ ሊሆንም አይገባም ።

የክርስቲያኖችን አጽም ማክበር ፣ አጽማቸው ያረፈባቸውን ቦታዎች በንጽሕና መያዝና መጠበቅ ይገባል ደጋግ አበው በሞት ሲለዩ በመካነ መቃብራቸው ተአምራት ይደረጋል ፣ ምልክት ይቆማል እንጂ ሐውልት አይሠራም ። ሥርዓተ አበው ልማደ አበው ፤ ሕገ አበው አይደለም ። ከቀደምት አበው ብዙዎች የሚቀበሩት በዋሻ በየቤታቸው አቅራቢያና በየግል እርሻ ማሳዎች ውስጥ ነበር ። የመታሰቢያ ሐውልት (ድንጋይ) የሚቆምላቸው ከዋሻዎችና ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ብለው ለሚቀበሩ ወገኖች ብቻ ነበር ። (ኢዮ ፣ ፳፩ ፣ ፳፱-፴)

ሰዎች በዚች ምድር ላይ በድህነትና በብልጽግና ኑረው በተፈጥሮ ግዴታ በሞት በሚለዩበት ጊዜ ራቁታቸውን ከናታቸው ማሕጸን እንደ ወጡ ራቁታቸውን ወደመሬት ስለሚመለሱ ሁሉም እኩል ናቸው ። በመቃብር ዓለም የከተሙ ሙታን ሁሉ ሀብታምና ድኃ ተብለው አይለዩም ፤ አይከፈሉም ። የዚህ ዓለም ባለጸጎች ከነበራቸው ሀብት የቻሉትን ያህል ተጠቅመው ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ምንም ሳይጠቀሙበት ለወራሽ (ለባዕድ) ትተውት ከሄዱት ሀብት ጥቂቱ ተቆንጥሮ ከዕብነ በረድ የሚቀረጽላቸው ሐውልት ወይም ከተለያየ ድንጋይ ተጠርቦ የሚሠራላቸው መቃብር ቤትና በብረት አጥር የሚከለለው የመቃብር ርስት ታላቅ ሊያደርጋቸው አይችልም ። ይህ ሁሉ ለቋሚ ዘመዶቻቸው ማባበያና ማታለያ አንዳንድ ጊዜም የትልቅነት ማሳያ የውድድር ምልክት እንጂ ሙታንን እንደ ማይጠቅም ሁሉ የሚያውቀውና የሚረዳው ነው ።

ሐውልት በመሬት ውስጥ ከሚደርሰው ሙስና መቃብር ( መፍረስ መበስበስ)አያድንም ። በሥጋ ወደመቃብር የወረዱ ሙታንን በዓለመ ነፍስ በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ሊያደርጋቸው የሚችለው የተሰጠውን ሕግ በመጠበቅ ፤ ትእዛዛትን በመፈጸምና አካሄዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር አድርገው የኖሩት መንፈሳዊ ሕይወት (ሃይማኖትና ምግባር) ብቻ ነው ።

ትልልቆችም የሚባሉት በዚህ ዓለም ሳሉ ችግረኞች ወገኖቻቸውን ንቀው ተጸይፈው ያልተመለከቱ ፣ ገንዘባቸው ባልሆነው ገንዘብ ወዳጅ ለመግዛት የቻሉ ፣ ያላቸውን ከሌላቸው ተካፍለው ሀብታቸውን ተገቢ ሥራ ላይ ያዋሉ ብቻ ናቸው ።

የክርስቲያኖች ሐውልት ፣ ቤተ ክርስቲያን ናት ፤ አማንያን በዓርባ በሰማንያ ቀን እየተጠመቁ ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማሕጸነ ዮርዳኖስ በመወለድ ከሥላሴ ልጅነትን ይቀበሉባታል ። ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ በሚለዩበትም ጊዜ የዕረፍት ቦታቸው ናት ። ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ፣ የመሥዋዕት ቦታ ከመሆኗም በላይ በተስፋ ትንሣኤ የሚታረፍባት ስለ ሆነች ሲያርፉ ደስ በሚያሰኝ ፣ ሲመላለሱባት ኀሊናን በሚሰብ ንጽሕና መጠበቅ ይኖርባታል እንጂ የሐውልት መከማቻ ልትሆን አይገባም ።

ሐውልት የሞተውን ወገን በቋሚ ዘንድ ስለሚያዘክር ፣ በዚሁ በም ድር ላይ እንዳለ አድርጎ ስለሚያሳስብ ትንሣኤን የሚያስረሳ አፍአዊ ምልክት (ከንቱ መታለያ) ነው ።

ሟች በሕይወት እያለ ሊገለገልበት የሚችለውን ወይም ለቀሪ ቤተ ሰብ የሚረዳውን አለያም ለቤተ ክርስቲያን መርጃና ለምግባረ ሠናይ ድርጅት ሊውል የሚገባውን ከፍተኛ ገንዘብ እያወጡ የጥርብ ድንጋይና የዕብነ በረድ ፣ የሸክላና የሲሚንቶ ፣ የኖራና የአሸዋ (ሐውልት) መሥራት በሐውልት ዙሪያ የብረትና የሽቦ አጥር ማጠር ፣ ለደካሞች ማረፊያና ለዳዊት ደጋሚዎች የማያገለግል የተዘጋ ቤት እያነጹ በመካነ መቃብር ግለኝነት (ባለርስትነት) መተናነቅ ሀብትን ንብረትን ማበላሸት ከመሆኑም በላይ ለሟችም ሆነ ለቋሚ የሚሰጠው አንዳች ጠቀሜታ የለም ። የአጸደ ቤተ ክርስቲያንን ውበትና ገጽታ ማበላሸት ፣ የክርስቲያኖችን የመካነ መቃብር ድርሻ ማጣበብ ነው ።

«የሐውልት ምረቃ» እየተባለ ከቤተ ክርስቲያን ያልተሰጠ እንግዳ ልማድና ከመንፈሳዊ ሥርዓት ውጭ የሚፈጸም ነው ። ለሞቱ ሰዎች ለሥ ጋቸው ትንሣኤን ፤ ለነፍሳቸው በጎ ዕረፍት ስጥ ለማለት ለምሕረትና ለይቅርታ በመካነ መቃብር ላይ ጸሎት ይደረጋል ። በሐውልት ዙሪያ ሕዝብ ሰብስቦ ሐውልቱን ግምጃ አልብሶ ጸሎተ አኰቴት ማድረስ ግን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የታዘዘም የተፈቀደም አይደለም ።

ሐውልት ከላይ በተገለጸው ምክንያታዊ ምልክትነቱና ታሪካዊ አመጣጡ አንጻር ከመታሰቢያነት አልፎ ከጊዜ ወደጊዜ መልኩን ፣ ቅር ጹንና መጠኑን እየለወጠ የትንሣኤን ተስፋ በሚታይ ምልክት የሚ ያጨልም ከሆነ ከጣዖት አምልኮ የሚያስቈጥር ግምት ያስከትላል ። ይህም አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን የተከለከለ ነው ።

«የተቀረጸ ምስል ወይም ሐውልት አታቁሙ . . .

በምድራችሁ ላይ የተቀረጸ ድንጋይ ፣ አታኑሩ » (ዘሌ ፡ ፲፱ ፡ ፳፰) መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዕብነ በረድና በሲሚንቶ ተለስነው በውጭ አምረው የሚታዩ የመቃብር ሐውልቶችን በግብዝነትና በረከሰ ተግባር ለተሞሉ ፈሪሳውያን ምሳሌ አድርጎ ጠቅሶአቸዋል ።

«በውጭ አምረው የሚታዩ ፣ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰ ትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላ ችሁ ፣ - - - - የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ ፣ የጻድቃንንም መቃብር ስለ ምታስጌጡና በአባቶቻችን ዘመን ኖረን በሆነስ በነቢያት ደም ባል ተባበርናቸው ነበር ስለምትሉ - - - በራሳችሁ ላይ ትመሰክራላችሁ» (ማቴ ፳፫ ፡ ፳፯-፴፩ )

የቀደሙት ክርስቲያኖች አባቶቻችን የሙታንን መታሰቢያ አስ መልክቶ በመካነ መቃብር ላይ የሚያቆሟቸው ምልክቶች አጸደ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስውቡና አገልግሎት የሚሰጡ ነበሩ የሚች ወገኖች

በቤተ ሰቦቻቸው መካነ መቃብር ላይ ልዩ ልዩ ዛፎችን ይተክላሉ ፤ መቃብር ቤቶችን ይሠራሉ ፤ ዛፎቹ ለአጸደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይውላሉ ፤ የመቃብር ቤቶችም ለዕቃ ቤት ፣ ለግብር ቤት ፣ ለጸሎት ቤትና ለደካሞች መጠሪያ ለእንግዶች ማረፊያና ለመሳሰለውም አገልግሎት ይውላሉ ። እነዚህም ቤቶች የሚሠሩት በቤተ ክርስቲያን ፈቃድና ንብ ረትነት የሌሎችን የመቃብር ድርሻ በማያጣብብ ሁኔታ ነበር ። በክርስቲ ያኖች መካነ መቃብር ዛፍ መትከልና የመስቀል ምልክት ማቆም የተ ለመደ ክርስቲያናዊ ትውፊት ነው ። ሁሉም ነገር በቤተ ክርስቲያን ፈቃድና ውሳኔ በዕቅድና በፕላን መፈጸም ይኖርበታል ።

ከዚህም ሌላ ቤተ ክርስቲያን መቃብር ቤቶችን ት/ቤት በማድረግ ሕፃናትን ታስተምርባቸዋለች ፣ ደቀ መዛሙርትን ታፈራባቸዋለች ፣ ካህናትን ታሠለጥንባቸዋለች ። የመምህራንና የደቀ መዛሙርት መጠለያ ዎችም እነዚሁ ቤቶች ናቸው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የትምህርት ማእከል ሆና ለመኖር የቻለችው እነዚህን በዙሪያዋ የሚሠሩ ቤቶች በየአ ጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ት/ቤቶች አድርጋ በመቆየቷ ነው ። ይህም እስከ ዛሬ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንደተጠበቀ ይገኛል ። ወደፊትም ተጠብቆ እንዲኖር የሚፈለገው ይኸው ትውፊት ነው ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በከተሞች በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሚሠሩ የመቃብር ቤቶች ይህን ትውፊት እየተዉ በመጠናቸው ከሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ የሚወዳደሩ ፤ የዐጸደ ቤተ ክርስቲያንን ውበት የሚያበ ላሹ የሌላውን መካነ መቃብር የሚያጣብቡ ፣ አብዛኛዎቹም ንብረትነ ታቸው በየግል እየሆነ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የማይሰጡ በመሆ ናቸው ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለብዙኃን ክርስቲያኖች ችግር ፈጥረዋል ።

ይህ ችግር እንዳይኖር ፣ መጥፎ ልማዱም እንዳይስፋፋ ማድረግና መቈጣጠር የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና የሰበካ ጉባኤ ሊቃነ መና ብርት ኃላፊነት ሆኖ ሳለ አብዛኞቹ የችግሩ ፈጣሪዎች ተባባሪዎች ሆነው በመገኘታቸው አሠራሩ በዚህ ዓይነት መልኩ እየቀጠለ ከሄደ የኢትዮ ጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ቆመው የሚጸልዩበትና ሲሞቱ የሚቀበሩበት ቦታ እንዳያጡ ፣ ያሠጋል ። ሕንጻ ቤተ ክርስቲያንን ለማስፋትና የልማት ድርጅቶችንም ለማቋቋም ስለማያስችል ከወዲሁ ሊታ ሰብበት ይገባል ። አድራጎቱ በሀብታሞችና በድሆች መካከል ልዩነት የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ ለቤተ ክርስቲያን አሠራር አመች አይደለም ። ልምዱም የመጣው ከሌሎች እንጂ ከአባቶቻችን የመጣ ባህልና ትውፊት ስላልሆነ እንዳይቀጥል የሚደረግበት መንገድ መፈለግ ይኖ ርበታል ። አበው የመካነ መቃብርን ጥበትና ችግር ተቋቁመው የኖሩት ከተወሰነ የጊዜ ገደብ (ሰባት ዓመት) በኋላ አዲሱን አስከሬን ከቈየው ጋር አዳብለው በመቅበር ነበር ። የመካነ መቃብር ችግርና በዚህም የተ ነሣ የሚታይ ውዝግብ አልነበረም ።

## መካነ መቃብር

የመካነ መቃብርን ይዘትና ታሪካዊ አመጣጥ በምንመለከትበት ጊዜ በዘመነ ብሉይ ሁሉ በየወገኑና በየዓፅመ ርስቱ ይቀበር እንደ ነበር እን ረዳለን ። በቅዱሳት መጻሕፍትና በቀኖና ቤተ ክርስቲያንም እንደተጻፈው የሚያምን ከማያምን፣ ብርሃን ከጨለማ፣ ታቦት ከጣዖት፣ አማንያን ከመና ፍቃን ጋር አንድነት ስለሌላቸው በአሪት በግዝረት ከአሕዛብ የተለዩ ክር ስቲያኖች በመቃብር እንደማይገናኙ ይታወቃል ።

አብርሃም እግዚአብሔርን በማመኑ ካላመኑት ቈላፋን (ያልተገረዙ) እንዲለይ፣ እነርሱም ከርሱ እንዲለዩ እግዚአብሔር ግዝረትን ምልክት

አድርጎ ሰጥቶታል ። አብርሃም በሃይማኖቱ በግብረቱ በዙሪያው ካሉት አሕዛብ ከመለየቱ የተነሣ የመቃብር ቦታውን ለይቷል ። ሚስቱ ሣራ በኬብሮን በሞተች ጊዜ የሀገሩን ባላባቶች የመቃብር ሥፍራ እንዲሰጡት ጠየቀ።የሀገሩም ተወላጆች ከነሱ መቃብር ቦታ በነፃ እንደሚፈቅዱለት ቃል ገብተውለት ነበር ። ነገር ግን አብርሃም የእግዚአብሔር ወገን በመሆኑ ሚስቱን በአሕዛብ መቃብር ሊቀብራት አልፈለገም ። ስለዚህም ኤፍሮን ከሚባል ሰው ርስት ላይ ለብቻው የመቃብር ቦታ በገንዘቡ ገዛ ። አብርሃም ለሚስቱና ለራሱ ፥ ለልጆቹና ለወገኖቹ የገዛው መካነ መቃብር (ርስት) ሌሎች የማይቀበሩበት ርሱ ብቻ በባለመብትነት የያዘው፤ለርሱ የጸና ነበረ ። በዚያ ነበር ሚስቱን ሣራን የቀበራት ። (ዘፍ ፡ ፳፫ ፡ ፩-፳ ፡ ኩፋሌ ፲፬ ፡ ፳፫-፳፯)

አብርሃምም ሲሞት በዚሁ የመቃብር ርስት ተቀበረ ። (ዘፍ ፡ ፳፭ ፡ ፰-፲፤ ኩፋሌ ፲፯ ፡ ፩ )

ይስሐቅም የሞቱ ጊዜ ሲቃረብ ሁለቱን ልጆቹን ያዕቆብንና ኤሳውን ጠርቶ "ልጆቼ ሆይ ! እኔ አባቶቼ በሄዱበት ጎዳና - - - ለዘለዓለም ወደምኖርበት ወደ መቃብር እሄዳለሁ አብርሃምም ለመቃብር በገዛው እኔ ለራሴ ባስቆፈርሁት በኬጢያዊው ሰው በኤፍሮን እርሻ ባለችው እጥፍ ነት ባላት ዋሻ በአባቱ በአብርሃም አጠገብ ቅበሩኝ አላቸው" (ኩፋሌ ፡ ፳፭ ፡ ፴፱) በሞተም ጊዜ ልጆቹ በኑዛዜው መሠረት ቀበሩት ። (ኩፋ ፡ ፳፯ ፡ ፩ )

ያዕቆብ በበኩሉ ጊዜ ሞቱ ሲቃረብ ልጆቹን ጠርቶ እንዲህ አላቸው «እኔ ወደ ወገኖቼ እሰበሰባለሁ በኬጢያዊው በኤፍሮን እርሻ ላይ ባለችው ዋሻ ከአባቶቼ ጋር ቅበሩኝ እርስዋም በከነዓን ምድር በመምሬ ፊት ያለች አብርሃም ለመቃብር ርስት ከኬጢያዊው ከኤፍሮን ከእርሻው ጋር የገዛት ባለድርብ ክፍል ዋሻ ናት ። አብርሃምና ሚስቱ ሣራ ከዚያ ተቀበሩ ፤ ይስሐቅና ሚስቱ ርብቃ ከዚያ ተቀበሩ፤ ከዚያም እኔ ልያን ቀበርኋት እርሻውና በርስዋ ላይ ያለችው ዋሻ ከኬጢ ልጆች የተገዙ ናቸው ። ያዕቆብም ኑዛዜውን ለልጆቹ ተናግሮ በፈጸመ ጊዜ እግሮቹን በአልጋው ላይ ሰብስቦ ሞተ ወደ ወገኖቹ ተከማቸ» ይላል ። ዘፍ ፵፱ ፡ ፳፱-፴፫) ።

የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍም ለወንድሞቹና ለልጆቹ ያደረገው ኑዛዜ "እግዚአብሔር ከግብፅ ምድር በአወጣችሁ ጊዜ አፅሜን በግብፅ ትታችሁ እንዳትሄዱ ከእናንተ ጋር ይዛችሁ ሂዱ" ሲል በመሐላ ቃል እንዳስገባቸው እንመለከታለን ። (ዘፍ ፡ ፶ ፡ ፳፭) በኑዛዜውም መሠረት ነቢዩ ሙሴ የዮሴፍን አፅም ይዞ እንደወጣ ተጽፎአል ። (ዘፀ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱)

ኑኃሚንም "ሠናይ ለብእሲ መቅብርቱ ውስተ ርስቱ ፦ ለሰው በርስቱ መቀበር መልካም ነው" ብላለች ። ሩት ፡ ፩ ፡ ፲፮ -፲፯ ።)

ከእግዚአብሔር የተነገረውን የማይቀበሉ የታዘዘውን የማይፈጽሙ ከትክክለኛው እምነትና ትምህርት ወጥተው ሐሳውያን ነቢያት በሚያመለክቷቸው የጥፋት መንገዶች የሚሄዱ ፥ ሁሉ ራሳቸው ነቢያትና መምህራንም ቢሆኑ የአባቶቻቸውን እምነትና ትምህርት ፥ ባህልና ትውፊት ፥ ልማድና ሥርዓት አቃለው ፡ የባዕዳንን መንገድ የተከተሉ ሐሰትን የሚያስተምሩ ሐሳውያን ፡ ኑፋቄን የሚዘሩ መናፍቃንም በአባቶች አፅመ ርስት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የመቃብር ውርስ ሊካፈሉ አይችሉም ። ድርሻም የላቸውም ። (፩ኛ ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፳—፳፫ ።)

እግዚአብሔር በቤቴልና በሰማርያ ከተሞች የነበሩትን በጣዖታቸ

ውና በመሥዋዕታቸው እግዚአብሔርን ያስቈጡትን ነገሥታትና ሠራ ዊት ጣዖቶቻቸውንና የጣዖት መሠዊያዎቻቸውንና መስገጃ ኮረብቶቻ ውን ሲያጠፉ፣ ከሀናት ጣዖቶቻቸውን ሲመታ ፤ በመቃብር የነበሩ አጽሞቻቸውን ሁሉ እያፈለሰ ሲበትነው አንዳንዶች ከእውነተኞች ነቢ ያት ተጠግተው በመቀበር ለመዳን ጥረት አድርገዋል ።

«ደግሞም በቤቴል የነበረውን መሠዊያ ፥ ፥ እስራኤልንም ያሳተ የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም ያሠራውን የኮረብታውን መስገጃ ፤ ይህን መሠ ዊያና መስገጃ አፈረሰ ፤ ድንጋዮቹንም ሰባበረ ፥ አድቅቆም ትቢያ አደረ ገው ፥ የማምለኪያ ዐፀዱንም አቃጠለው ። ኢዮስያስም ዘወር ብሎ በተራ ራው የነበሩትን መቃብሮች አየ ኢዮርብዓምም በበዓል ጊዜ በመሠዊያ አጠ ገብ ሲቆም እነዚህን ነገሮች የተነበየ እግዚአብሔር ሰው እንደ ተናገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል ልኮ ከመቃብሮቹ አጥንቶቹን አስወጣ በመሠ ዊያውም ላይ አቃጠላቸው አረከሰውም ። ዘወርም ብሎ ወደ ተናገረው ወደ እግዚአብሔር ሰው መቃብር ዓይኖቹን አቅንቶ ፦ ያ የማየው የመ ታሰቢያ ምልክት ምንድን ነው ? አለ ። የዚያችም ከተማ ሰዎች ከይ ሁዳ ወጥቶ በቤቴል መሠዊያ ላይ ይህን ያደረግኸውን ነገር የተናገረው የእግዚአብሔር ሰው መቃብር ነው ብለው ነገሩት»።(፪ ነገ ፥ ፳፫ ፥ ፲፭-፲፯)።

ይህን በተመለከተ ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንዱ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ የሚከተለውን መወድስ ቅኔ ተቀኝተዋል ።

«እንትኰ በለሰ እመ በላዕክሙ
ወተጋባእክሙ ደርገ ኀበ ሀለወ ገደላ
እንስርተ ዲዮስቆሮስ ሊቅ ሊቃውንተ ጐንደር ገሊላ
እሞትክሙ ሞተ ዘኢዩኤል
ወእምየብስተ እስከ ፍጻሜሁ ዜናክሙ ስግላ
በሊዐ እከለ ባዕድ እስመ ውእቱ ዘበርአሰ ነቢይ አብቈለ
አፈ አንበሳ ሐቅል አሜከላ ።
ማዕዷኒ እንዘ ንዉር በትፋዐ ጽልዕ መሐላ ፥
በዐልተ በለስ እፎኑመ ጸውዐተክሙ ለበዓላ
ይገብሩ ኀቡረ በዐለ ትፍሥሕት ወተድላ ፤
ዶርሆ ምስለ እንቁ ወበግዕ ምስለ ተኩላ ። »

ሌላውም ሊቅ

« - - - - ዐፅመ ነቢየ ቤቴል ድኅነ

ምስለ ዐፅመ ባዕድ

እንዘ ነፍሱ ትውዒ በነድ » በማለት ተቀኝተዋል ።

ዙፋኔ በረድኤት የሚዘረጋበት ፥ እግሮቼ የሚቆሙበት የሚመላ ለሱበት በእሥራኤል ልጆች መካከል ለዘለዓለም የማድርበት፣ጸንቼ የምኖ ርበት ቦታ ይህ ነው ከእንግዲህ ቤተ ጣዖት አያሰኙት ። - - በመቃብር ቤታቸው ፥ በምሥዋዐ ጣዖታቸው አያርክሱት ፥ መድረካቸውን በመድ ረኬ ፥ መቃናቸውን በመቃኔ አንፃር አድርገው ፤ በመካከል ቅጽር ሠርተው እንዳረከሱት አያርክሱት ። ከሰሎሞን ጀምሮ የነበሩ ነገሥታት ስመ መቅ ደሴን ወደው በሠሩት በኃጢአታቸው በጣዖታቸው አረከሱት እኔም እን

ዳዘንሁ አልቀረሁም ተበቅየ አጠፋኋቸው ። ዛሬ ግን ጣዖታቸውን እስከሬናቸውን ከኔ ያርቁ የተቀበረውን ያፍልሱ ዳግመኛ አይቅበሩ ። (ሕዝ ፵፫ ፡ ፯—፱) ።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ማንኛውም ሕዝብ እንደየእምነቱ የተለየ የመቃብር ቦታ እንደነበረውና እንዳለው ነው ። የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓትና ቀኖና ከሌሎች የተለየ ነው ። በትምህርተ ሃይማኖት ፣ በምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን ፣ በሥርዓተ አምልኮት የማይመስሉን ሁሉ በመካነ መቃብር አንድነት ሊኖራቸው አይችልም ። ይህም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተደንግጓል ። በፍትሐ ነገሥት በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፭ ቁ ፲፬ "ይዕቀብዎሙ ለአናቅጸ ቤተ ክርስቲያን ከመ ኢይባኡ ኀቤሃ ዕደው እለ ኢኮኑ ምእመናነ አው ምእመናን ውጉዛን እምሱታፌ ምሥጢር ቅድስት" ይላል ። ይህም ማለት በእምነት ልዩነት ያላቸው ሰዎች ወይም በክህደት ሥጋውንና ደሙን ከመቀበል የተወገዙና በምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን አንድነት የሌላቸው ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመግባት ይከልከሉ" ማለት ነው ።

በሌላ በኩል በማወቅና ባለማወቅ ከእውነተኛው የእምነት መንገድ የወጡ ሰዎች በንስሐ ከተመለሱ ቤተ ክርስቲያን እንደምትቀበላቸው ይኸው የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ሲያስረዳ "የራሱ ክህደት ብቻ አልበቃው ብሎ ባልንጀራውን ከሃይማኖቱ እስኪያወጣው ድረስ ለማስካድ ምክንያት የሆነው ሁሉ ንስሐው የጸና ይሆናል ።

አስቀድሞ የካደ ፣ በሃይማኖቱ ያልጸና ሰው ወደ እውነተኛው ሃይማኖት በተመለሰ ጊዜ ብዙ ቀን በንስሐ ይኑር ፣ በፍጹም ልቡ ቢመለስ ፣ ሊቈርብም ቢፈልግ ያቍርቡት ። ሕማም ቢታመም ግን ለሞትም ቢደርስ በዳነ ጊዜ ወደንስሐው ይመለስ ዘንድ ሥጋውንና ደሙን ያቀብሉት ። እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ብዙ ዘመን ንስሐ ከገቡ በኋላ በክብር ይቀበሉአቸው ከምእመናን ጋር አንድ ይሁኑ ሕጋችን የርኅራኄና የይቅርታ ነውና" ብሏል ።

የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች መካነ መቃብር በእምነት አንድ ለሆኑት ብቻ የተወሰነ መሆኑን በሚያስረዳው አንቀጽም "የሰማዕታትን ዓፅም በቤተ ክርስቲያንና በገዳም ያኑሩ ሥጋቸው ከተቀበረበት ቦታ ለድውያንና ለታመሙ ጥቅምንና ድኅነትን ለሚሹ ሰዎች ድኅነትና ጥቅም ይሆን ዘንድ ንጹሐን የሚሆኑ የእነዚህን ዓፅም የሚሳደቡትንና የሚያረክሱትን ሰዎች ግን ከእሱ በሚደረገው ተአምራት ድውያንን በማዳን በሥጋና በነፍስ የታመሙትን በመፈወስ ከእነሱም ሰይጣንን በማስወጣት እግዚአብሔር ያሳፍራቸዋል ። በሰማዕታት በዓል የሚሰበሰቡትን ሰዎች የሚንቅ ሰው ትዕቢትን የተመላ ነውና የተወገዘ (የተለየ) ይሁን" በማለት ያለውን ሁኔታ ይገልጻል ። ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ ፳ ቍ ፣ ፯፻፶፭-፯፻፷፩ በአንቀጽ ፳፪ ላይ "ወያንብርዎ ለሥጋሁ ውስተ መካነ ክቡር በአግዋረ ሥጋ ንጹሕ ዘስንዕው ምስሌሁ ውስተ ግዕርጉ፡- በሃይማኖትና በግዕርግ ከሚመስለው ፣ ንጹሐን የሆኑ የቅዱሳን ሥጋ ባለበት በከበረ ቦታ በቤተ ክርስቲያን ያኑሩት" ይላል ። ቤተ ክርስቲያን የደጋግ አበውንና የቅዱሳንን ዓፅም በየገዳማቱ የክብር ሥፍራ ሰጥታ የምታኖረው በዚህ መሠረት ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ምእመናን ዓፅመ ርስት ቤተ ክርስቲያን ናት ። ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን እምነው ፣ በቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ወላዲተ እግዚአብሔር፣ በቅዱሳን መላእክት ፣ በጻድቃንና በሰማዕታት አማላጅነት የሚከተሏት ሁሉ ተሰብስበው ትምህርተ ሃይማኖት የሚማሩባት አምልኮተ እግዚአብሔርን የሚፈጽሙባት ፣ ሥጋውንና ደሙን የሚቀበሉባትና የሚጸልዩ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት

The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order

www.ethiopianorthodox.org

ባት ፤ ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ በሚለዩበትም ጊዜ ዓፅማቸው የሚያርፍ ባት ሥጋቸውንና ነፍሳቸውን አንድ አድርገህ አስነሣ" ተብሎ በሚ ቀርበው ጸሎት የክብር ትንሣኤን የሚጠብቁባት መካነ ዕረፍት ናት ።

በክርስትና ስም በዘመናችን በዓለሙ ላይ የዘመቱበት መናፍቃንና ሐሳውያን መምህራን እንደሚሉት ሰዎች ሞተው ፤ በመቃብር ፈርሰው አፈር ትቢያ ሆነው አይቀሩም ። ሥጋቸው በመቃብር አርፎ የሚቈየው ሙታንና ሕያዋንን አንድ አድርጎ የሚገዛየሥነ ፍጥረት ባለቤት ልዑል እግ ዚአብሔር ለሁሉ እንደየሥራው ዋጋውን ለመክፈል እስከሚመጣበት ጊዜ ብቻ ነው ። እስከዚያውም ቢሆን በቀና ሃይማኖትና በበጎ ምግባር የኖሩ ክርስቲያኖች ነፍሳት እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ባዘጋጃት በተድላ ገነት ያርፋሉ ። በእግዚአብሔር ረድኤትም ተጠብቀው ይኖራሉ ። በመ ሆኑም በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር የሚያርፉ የክርስቲያኖች ዐፅም የከበረ ነው ። የሥጋቸው መካነ ዕረፍት ቤተ ክርስቲያንም የከበረች ናት ። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ሕዝበ እግዚአብሔርን ወክሎ "ዕፀ ዘይት በቤተ እግዚአብሔር ያማረ የተወደደ እንደሆነ እኔም ያማርሁ የተወደድሁ ነኝ" ብሏል ። (መዝ ፡ ፶፩ ፡ ፰) ይኸው ነቢይ በሌላው ። « - - - ጻድቅ እንደዘንባባ ያፈራል ፤ በደጋ እንደተተከለ ዝግባ ይሆናል ፤ (ጻድቃን) በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክለዋል ። በዐጸደ ቤተ ክርስቲያን ይበ ቅላሉ (ይነሣሉ) ።

ያን ጊዜ በለመለመ አካል ይኖራሉ ደስተኞችም ሆነው ይኖራሉ » ብሏል (መዝ ፡ ፺፩ ፡ ፲፪) ።

ክርስቲያኖች በፈጣሪያችን መመለኪያና መመስገኛ ቦታ በቤተ መቅደስ ዙሪያ እንደተተከሉ እንደዝግባና እንደ ዘንባባ ዛፎች ናቸው ። በበጎ ዘመን እንደሚኖሩ ሕፃናትና አረጋውያን በጎ ሕይወት ይኖራሉ ። ሕፃን ወተት ፍትፍት ሳያጣ አረጋዊ መውጣት መውረድ ሳይኖርበት እንደሚኖሩ ከመከራው አርፈው በተድላ ይኖራሉ፤ ፈጣሪያችን እግዚአ ብሔር የባሕርይ አምላክ እንደሆነ ይናገራሉ ያስተምራሉ ፤ ይህ ለምእ መናን ሁሉ ደስታቸው ነው ። ከዚህ ዓለም ሲለዩ በሚያገኙት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በሕይወተ ሥጋ በሚኖሩበት ጊዜ የሚናፍቁት ሕይወት ነው ።

«እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እሷንም እሻለሁ በሕ ይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን አይ ዘንድ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ» በማለት ሕዝበ እግዚአብሔር በሥጋም ሆነ በነፍስ ከእግዚአብሔር ቤት የተለየ መኖሪያ እንደሌላቸው አመልክቷል (መዝ ፳፮-፬) ።

ጠቢቡ ሰሎሞን "ታኅተ ጽላሎቱ ፈተውኩ ወነበርኩ በእግዚአብሔር ቤት ጥላ ሥር መኖርን ወደድሁ" ያለው ስለዚህ ነው (መሐልይ ፪ ፡ ፫)

በመካነ መቃብራችን መስቀል አለ ። መስቀል ለኛ የሕይወት ጥላ ነው ። በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን አስገኝቶልናል ብለን እናምናለን። በምንሞትበትም ጊዜ እንደቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና በጸሎተ ፍትሐት፥ በዕጣንበመሥዋዕት፥እንሸኛለን አሁን በመካነ መቃብር እንዛመድ የሚሉን ግን ይህን ሁሉ አይቀበሉም ፤ አይፈጽሙም «ሥጋውን ደሙን መታሰ ቢያ ነው» ይላሉ ። እኛ ግን የምንቀበለው ሥጋውን አማናዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ፤ ደሙንም አማናዊ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ብለን ነው ። ባጠቃላይ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንገናኝም።ስለዚህም በ ትምህርተ ሃይማኖትና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የማይመስሉንን በምሥ ጢራተ ቤተ ክርስቲያን ከኛ ጋር አንድነት የሌላቸውን በመካነ መቃብር አንቀበልም ።

ስለዚህ ይህ ልዩነት በመካከላችን መኖሩ እየታወቀ በአሁኑ ወቅት የመጡ ሃይማኖት ተከታዮች በየቦታው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ውስጥ መካነ መቃብር ይሰጠን በማለት የሚፈጥሩት ውዝግብ ለዘመናት በማኅበራዊ አንድነቱ ጸንቶ በሰላም የኖረውን ሕዝብ ለመከፋፈልና ለማበጣበጥ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም ።

በዘመናችን ጊዜ ወለድ የሆኑ የልዩ ልዩ እምነት ተቃዋሞች የኑፋቄ ደጋፊዎች በሆኑ አንዳንድ የወቅቱ የአካባቢ ባለሥልጣኖች እየተረዱ በሀገሪቱ ውስጥ የነበረውንና የቈየውን የሕዝበ ክርስቲያን ሰላማዊ ሕይወት ለማናጋት በግልና በቡድን ከሚያካሂዱት ዘመቻ የተነሣ በመካነ መቃብር ምክንያት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በብዙ ቦታ ችግር እየተፈጠረ ነው ። የቤተ ክርስቲያናችን ተከታዮች ካህናትና ምእመናንም ለዘመናት ሲከተሉት በቈዩት እምነታቸውና የኅሊና ነጻነታቸው ላይ በሚደረገው ዘመቻ እጅግ እየተቸገሩ ነው ። ለርስ በርስ ግጭትና ለከረረ ጥላቻ በሚጋብዙ የተንኰል ወጥመዶችም ብዙ ጊዜ ይፈተናሉ ። የዚህም ሁሉ ችግር ምንጩና መነሻው ፤

፩/ አንዱ የሌላውን እምነት ተከታይ በመስበክና በማታለል እንዳይቀስጥ (እንዳይሰርቅ) በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የተላለፈውን የጋራ ውሳኔ በመጣስ የተለያዩ የምዕራብ አገሮች ሚሲዮናውያን በግልና በቡድን እያሴሩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያራምዱት የጥፋት ዘመቻ ነው ።

፪/ በቤተ ክርስቲያኒቱ የሰበካ ክልል (አጥቢያ) ውስጥ እየገቡ ተከታዮቿ ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንዳይሄዱ ያሰናክላሉ ።

፫/ በተለያዩ ምክንያቶች በሚደርሱ ጊዜያዊ ችግሮቹ ሰበብ እየገቡ በምግባረ ሠናይ ስም በሚያቀርቡት ርዳታ ሕዝበ ክርስቲያኑ እምነቱን ፤ ታሪኩንና ባህሉን እንዲለውጥ በመደለልና በማታለል ፤ አንዳንድ የሥራ መስኮችና የነፃ ትምህርት ዕድል እየሰጡ በመውሰድ ፤

፬/ በየአውራ መንገዶች በመዘዋወርና በየግል ቤቶች ዘልቀው በመግባት ሕፃናትንና ሴቶችን ከቤተሰቡ እምነት በመለየት

፭/ ቤተ ክርስቲያንን በመንቀፍ ፤ እምነቷን በማጥላላት የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ በማዛባትና የተለያዩ የማሳሳቻ ጽሑፎችን በማሰራጨት ።

፮/ ለቤተ ክርስቲያን አበው ፤ ካህናትና ጠንካራ እምነት ላላቸው ምእመናን ያልሆነ ስም እየሰጡ በማስጠላት በፍቅር ፤ በሰላምና በቤተሰብ መንፈስ የኖረውን ሕዝብ ለማለያየት አልፎም ለፀብና የርስበርስ ግጭት እያነሳሱት ነው ።

- በሕይወት እያሉ ጠልተው በማስጠላት ነቅፈው በማስነቀፍ በተለዩአት ቤተ ክርስቲያን የመቃብር አንድነት (ድባልነት) መጠየቃቸው ሕዝበ ክርስቲያንን እጅግ እያስቆጣውና መብቱን ለማስከበር በሚያደርገው መከላከል ብዙ ዓይነት አወዛጋቢ ችግር እየተፈጠረ ነው ።

እጅግ የሚገርመው «ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮኻል» እንዲሉ ሚሲዮናውያንና ዘርፎቻቸው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ እየገቡ ሃይማኖቷንና ሥርዓተ አምልኮቷን በማጥላላት ቤተ ክርስቲያንን በመንቀፍ የአገልጋዮች ካህናትን ስም በማጉደፍ ሕዝቡን ከሕዝብ የሚያለያዩና ሰላምን የሚነሡ ራሳቸው ሆነው ሳለ ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርና ለሃይማኖት ቤተሰቦቻቸው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያቀርቡት ክስና ስሞታ ነው ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መካነ መቃብር ሊያገኙ የሚገባቸው ፤

፩/ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ያመኑና የተጠመቁ

፪/ በቤተ ክርስቲያኒቱ መመሪያ በቃለ ዓዋዲው ደንብ መሠረት የተመዘገቡና ዐሥራት በኵራት በማውጣት ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን የሚያሟሉ ።

፫/ የነፍስ አባት ያላቸው በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን እየኖሩ ሥጋውንና ደሙን የሚቀበሉና ይህን በመሳሰለው ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት የሚፈጽሙ ናቸው እንጂ ማናቸ ውም በስመ ክርስቲያን አይደለም ።

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ መካነ መቃብር ያላት አቋም በቅዱሳት መጻሕፍት በተ ጻፈውና በተደነገገው መሠረት የጸና ነው ። በመሆኑም ፤

፩ . የተለያዩ እምነት ተከታዮች ያልተለመደና እንግዳ ሥርዓት በመፍጠር በሚያካሂዱት ዘመቻ በመካነ መቃብር ምክንያት በየጊዜ ውና በየቦታው በሚያነሣሡት ሁከት ሕዝቡን ከመለያየት ፣ ሰላምን ከማ ደፍረስ እንዲቆጠቡ ።

፪ . የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አንዱ በሌላው የእምነት ክልል እየገባ እንዳይቀስጥ ፤ እንዳይበርዝና እንዳይከልስ በጋራ ያወጣ ውን ድንጋጌ በማክበር የመጡ እምነት ተከታዮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮችን ከማወናበድ ተዐቅበ እንዲያደርጉ ፤

፫ . የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርም ስለዚሁ ጉዳይ የወ ጣውን ሕግና የጋራ ድንጋጌ እንዲያስከብርና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያንን አቋዋምና በየጊዜው በሚሰዮናውያን የሚደርስባ ትን ችግር ተገንዝቦ ችግሩን በሚፈጥሩት የእምነት ክፍሎች ላይ አስፈ ላጊውን ርምጃ እንዲወስድ ።

፬ . በመንግሥትም በኩል ጉዳዩ የሕዝቡን አንድነት የሚ ከፋፍልና ሰላማዊ ኑሮን የሚያናጋ ስለሆነ ትኩረት እንዲሰጠው ከሕግ አኳያ አስፈላጊው ገደብ እንዲደረግለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አበክራ ታሳስባለች ።

፭ . የቤተ ክርስቲያናችን አገልጋዮች ካህናትና ተከታዮች ምእ መናንም ለዘመናት ተጠብቆ ሲሠራበት በቆየው ባህልና ተከብሮ በኖ ረው ሥርዓት መሠረት ቤተ ክርስቲያናቸውንና መካነ መቃብራቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲያስከብሩ የተለያየ እምነት ተከታዮች በየመንደሩ ሠርገው በመግባት በቤተ ክርስቲያናችን ተከታዮች ላይ የሚያካሂዱትን የማሳሳት ዘመቻ ነቅተው እንዲጠብቁና በተሳሳተ መንገድ ተወስደው የችግር ፈጣሪዎች ተባባሪ የሆኑል ጀፓቸውንም አጥብቀው እንዲቈጣጠሩ፤

፮ . መላው አብያተ ክርስቲያናት በዐውደ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ የሚታየውን የሸቀጥ ገበያ እየተቈጣጠሩ ከቤተ ክርስቲያን ያልተፈቀዱ ልዩ ልዩ መጻሕፍትና ጋዜጦች መጽሔቶችና እትሞች ሥዕሎችና መስቀ ሎች የመዝሙር ክሮችና ሌሎችም አልባሌ የሸቀጥ ዕቃዎች በቅጽረ ቤተ ክርስቲያንና በዐውደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይሸጡ ሕጋዊ ክትትል እን ዲያደርጉ ።

፯. ዐጸደ ቤተ ክርስቲያንና መካነ መቃብር በንጽሕና እንዲጠበቁ አስፈላጊውን ሁሉ እንዲፈጸሙ ጥብቅ መመሪያ ታስተላልፋለች ።

# ተዝካርና ቍርባን

«ተዝካር » የሚለው ሥርወ ቃል «ተዘከረ አሰበ» ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው ። ተዝካር ማለትም መታሰቢያ ማለት ነው ። መታሰቢያው የሚደረገው ለሙታን ሲሆን ፣ የሚቀርበው በጸሎት በመሥዋዕት በመብራት ፣ በማዕጠንትና በምጽዋት ነው ።

ለተዝካረ ሙታን የሚቀርበው ጸሎት ፣ ምጽዋትና መሥዋዕት ለሞቱ ሰዎች ድኅነትን ፣ ለቋሚዎች በረከትን ያስገኛል ። መታሰቢያነቱም በፈጣሪና በፍጡራን ፣ በሕያዋንና በሙታን መካከል ጸንቶ የሚኖር ነው ።

ለሙታን የሚደረገው መታሰቢያም ከዕለተ ሞት እስከ ዓመት ከዚያም በላይ ሲሆን

፩/ በዕለተ ሞት
፪/ በሣልስት
፫/ በሰባት
፬/ በአሥራ ሁለት (በአሥራ ዐራት)
፭/ በሠላሳኛው ቀን
፮/ በዓርባኛው ቀን
፯/ በሰማንያኛው ቀን
፰/ በስድስተኛው ወር (መንፈቅ)
፱/ በሙት ዓመት ነው ።

ይህም ሥርዓት ከቅዱሳት መጻሕፍት ከሐዋርያትና ከሠለስቱ ምዕት ቀኖና የተገኘ እንጂ ልበ-ወለድ አይደለም ። እነዚህም የመታሰቢያ ዕለታት ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተያያዘ ምሳሌና ትርጉም አላቸው ።

ይኸውም ፩/ ዕለተ ሞት የሟች ነፍስ ከሥጋ የምትለይበት ወደአስገኚዋ ወደ እግዚአብሔር የምትመለስበት ፣ ቅድመ እግዚአብሔር ስጊድ የምታቀርብበት ፣ «ሥጋ መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ» በተባለው መሠረት ወደመቃብር የሚወርድበት በመሆኑ ነው ። (ዕገ ፣ ሉቃ ፣ ፮ ፣ ፲)

፪/ ሣልስት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ቆይቶ መነሣቱን የሚያመለክት ነው ። ይህንንም «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሦስተኛው ቀን እንደተነሣ እናንተም ለሞቱ ዘመዶቻችሁ በሦስተኛው ቀን ዳዊት አስደግሙችሁ ፣ ጸሎት አስደርጋችሁ መታሰቢያቸውን እህል ውኃ ስጡላቸው» በማለት በፍትሐ ነገሥት ተጽፎአል ይህንንም መታሰቢያ በፍጹም መንፈሳዊ ትርጉሙ የሟች ቤተሰብ በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው በጸሎትና በመሥዋዕት እንዲፈጸም ሲያስደርጉ ሲገባ ወዳጅ ዘመድና ጎረቤት በሟች ቤት በማለዳ እየተሰበሰበ የሚደረገው ልቅሶና ኀዘን ፣ ሙሾና ዕንባ የሚደገፍ አይደለም ። ከሥርዓትም የወጣ ነው ። ጉዳትና መንገላታትን ካልሆነ በቀር የሚያስገኘው ውጤትም የለውም ። በቤተ ክርስቲያንም ቢሆን በመካነ መቃብሩና በማርገጃ ላይ የሚደረገው ከሥርዓት የወጣ ልቅሶ የተከለከለ ነው ።

፫/ ሰባተኛ ቀን ጌታ ሥራውን ሁሉ ፈጽሞ ያረፈበት ስለሆነች ሰባት ቍጥር በዕብራውያን አቈጣጠር ፍጹም ስለሆነ ፣ በሱባኤም

ሰሉስ ሰባት ቀንአንድ ሱባኤ ስለሆነ ሱቱኤል ዕዝራም በራእይ እንዳየው ነፍስ ከሥጋ ተለይታ ወደፈጣሪዋ በምትመለስበት ጊዜ መላእክት ሰባት ቀን ገነትንና ሲዖልን አዙረው አሳይተው በሚገባት ቦታ የሚያሳርፏበት ስለሆነ በዚሁ ዕለት ለሙታን መታሰቢያ ጸሎትና ቍርባን ይደረጋል ። ዕዝራ ሱቱ ፡ ፯ ፡ ፹፩-፹፪)

፲፪/ አሥራ ሁለት (አሥራ አራት) በዚህም ዕለት ለሙታን መታሰቢያ እንዲደረግ በሐዋርያት ሲኖዶስና በፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ ተገልጾአል ።

፴/ ሠላሳ ፡- በሠላሳኛው ቀን የሚደረገው መታሰቢያም ሕዝበ እሥራኤል ሙሴና አሮን በሞቱ ጊዜ እስከ ሠላሳ ቀን በኀዘን እንደአሰቡአቸው እኛም በሠላሳኛው ቀን ለሙታን መታሰቢያ እንድናደርግላቸው የተጻፈ ስለሆነ ነው ። (ዘኍ - ፳ ፡ ፳፱) ። (ዘዳ ፡ ፴ ፡ ፰)

፵/ ዓርባ ፡- ስለ ዓርባ ቀን የሚታተቱ ብዙ ምሥጢራት አሉ አዳም በተፈጠረ በዓርባኛው ቀኑ ልጅነትን አግኝቶ ገነት ገብቷል (ኩፋ- ፬ ፡ ፱)

ሰው በናቱ ማሕጸን ሲፈጠር ተስዕሎተ መልክዕ ይፈጸምለታል (ቅ ፡ አትና)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በዓርባኛ ቀኑ ዐርጓል ።

በዚሁ መሠረት ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው «ልጄ ሆይ የተጠመቀ ክርስቲያን ሰው ከሞተ በኋላ ነፍሱ በዓርባኛው ቀን በፈጣሪዋ ፊት ቆማ ዋጋዋን እንደምታገኝ ዕወቅ» በማለት ለሙታን የዓርባ ቀን መታሰቢያ (ተዝካር) እንዲደረግ ጽፈዋል ።

፹/ ሰማንያ ፡-እናታችን ሔዋን በተፈጠረች በሰማንያኛው ቀን ገነት የገባችበትን የሚያሳስብ ሲሆን ለሞቱ ወገኖች በዚሁ ቀን መታሰቢያ ጸሎት መሥዋዕትና ምጽዋት እንዲደረግ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተወስኖአል ። (ኩፋሌ ፬ ፱-፲)

፻፹/ መንፈቅ ፡ - በስድስተኛው ወር እንደዚሁ ለሙታን መታሰቢያ እንዲደረግ በፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ ተደንግጎአል ። ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፳፪ ።

፻/ ዓመታት ፡- ከላይ በተገለጸው መሠረት ከዚህ ዓለም በሞት ለሚለዩ ሰዎች ከዕለተ ሞት እስከ መንፈቅ መታሰቢያ የሚደረግበትን ምክንያትና ትውፊት ተመልክተናል ። በዚሁ መሠረት በሙት ዓመትም መታሰቢያ ይደረጋል ። ከዚህም በኋላ በየዓመቱ የጸሎት ፡ የመሥዋዕትና የምጽዋት መታሰቢያ ሲደረግ ይኖራል ። በክርስትና ትምህርት ከዕለተ ልደት እስከዕለተ ሞት ይከብራልና ። ባጠቃላይም ነፍሳተ ሙታንን ለማሰብ ቤተ ክርስቲያናችን በየዓመቱ ኅዳር ፳፩ ቀን በመላው አብያተ ክርስቲያናት ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ ደንግጋለች ።

የቤተ ክርስቲያናችን ሕግና ሥርዓት ሁሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት የተያያዘ ነው ። በቅዱሳት መጻሕፍት ተዝካረ ሙታንን አስመልክቶ ብዙ ተጽፎአል ።

ነቢዩ ዳዊት «ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ ፡- የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል» ብሏል ። (መዝ ፡ ፻፲፩ ፡ ፮/ ልጁ ሰሎሞንም «የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው» በማለት በምሳሌው ጽፎአል ። (ምሳ- ፲ ፡ ፯) ።

ስለሞቱ ዘመዶቻችን የምናለቅሰውና የምናዝነው የሞቱ ወገኖቻችን ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር መለየትና መራቅ እንዳያገኛቸው በዚያም ኀዘንና ልቅሶ (ትካዜ) እንዳይደርስባቸው በምጽዋትና በጸሎት በማሰብ እንጂ ከኛ ስለተለዩ ሊሆን አይገባም ። በዚህ ፈንታ ግን «የብስጭት ኀዘን ወደልቡናህ አታግባ ፤ የብስጭት ኀዘንን ካንተ አርቃት ፣ ድኅነት እንደሌለበት ዕወቅ ፣ ራስህን ታሳዝናለህ ፣ ነገር ግን የምትጠቀመው ነገር የለም ። የሞተ ሰውስ ዐረፈ ። ነገር ግን ነፍሱ ታርፍ ዘንድ ተዝካር አውጣለት ከዚህ በኋላ ልቅሶህን ተው» ብሎ ሢራክ እንደጻፈ ለሞቱ ዘመዶቻችን በተወሰነው በታዘዘው መሠረት መታሰቢያቸውን ልናደርግላቸው ይገባል ።

ስለዚህም ካህናት በማይገባው ሳይሆን በሚገባው ኀዘንና ልቅሶ ለሙታን ሊጸልዩ ፣ በመሥዋዕትና በቍርባን ሊያስቡአቸው ይገባል ። ካህናት ለሙታን የሚገባውን ጸሎት (ጸሎተ ፍትሐት ) በሚያደርሱበት ጊዜ መላእክት የሙታንን ነፍሳት ተቀብለው ለማሳረግ ይወርዳሉ ። የሟች ነፍስ ንጽሕት የሆነች እንደሆነ ደስ ይሰኛሉ፤እግዚአብሔርንም «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ፣ በምድርም ለሰው ልጅ በጎ ፈቃድ» እያሉ ያመሰግናሉ ። የኃጥዕ ነፍስ ከሆነች ስለሷ እግዚአብሔርን ይለምናሉ ፣ ይማልዳሉ ። «የቅዱሳን መላእክት ምሥጋናቸውና ደስታቸው የሰው ድኅነት ነው» ተብሎ በመጽሐፈ ግንዘት ተጽፎአል ።

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ለሞቱ ሰዎች በምጽዋት ፣ በመሥዋዕት መታሰቢያ እንዲደረግላቸው ታስተምራለች ነገር ግን መታሰቢያው የሚደረገው በሃይማኖት ጸንተው ቀና ምግባር ይዘው በትክክለኛ ክርስቲያናዊ ሕይወት ኑረው ለተለዩ እንጂ ከሃይማኖት ወጥተው ከሥነ ምግባር ርቀው ለሚለዩ ሰዎች አይደለም ። ለሙታን መታሰቢያ ማድረግ የሚገባቸውም እንኳ በትምህርተ ሃይማኖት ፣ በአምልኮተ እግዚአብሔር የጸኑ ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀው በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖሩ መሆን ይኖርባቸዋል ።

ይህንንም «ስለሞቱ ሰዎች ነፍሳት ከገንዘባቸው ለድሆችና ጦም አዳሪዎች ይመጽውቱላቸው እንደዚህ አድርጉ ብለን የምናዝዛችሁም በሃይማኖት ጸንተው ለሞቱ ሰዎች እንጂ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ሰዎችስ በዓለም ያለውን ገንዘብ ሁሉ ቢመጸውቱላቸው ምንም ምን አይጠቅማቸውም ። እንደዚሁም ከሃድያንና መናፍቃን ይህንን እንዲያደርጉ አናዝዛቸውም» በማለት ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ገልጸዋል ።

---

**አዘጋጆች**

፩/ መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ኃላፊ

፪/ ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዩ
የትምህርትና ማሠልጠኛ መምሪያ ኃላፊ

፫/ መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ
የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ

፬/ መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት መምህር ፣